# አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ከአማርኛ ትርጉምና አቻዎቻቸው ጋር

ለ

፫ኛው ሽህ

3rd Millennium

መባቻ

በ

አፈወርቅ ታረቀኝ

መስከረም ፳፻፩ - 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

www.debelo.org

## አእኰቶ - ምስጋና

## ለእግዚአብሔር!

ጽሑፉን በማንበብ ማሻሻያ ሀሳብ የለገስከኝ መምህር እየለ እሻግሬና አስተያየት የሰጠኸኝ አቶ ታምሩ አሸቴ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

«አንድ እጣት ቁንጫ አይገድልም» እንዲሉ በሀሳብ ያበረታታችሁኝ ሁሉ ተባረኩ! ቡሩክ ሁኑ!

©

ያዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

All wrights reserved.

የመጀመሪያ እትም ፳፻፰ - 2008 ዓ.ም

እርማት፣ አስተያየት፣ . . . መስጫ

+251 0911 44 46 08

afetar2030@yahoo.com

## ማስታወሻነቷ

መልአከ ሕይወት አባ ውባገኝ ባንቴ በ1911ዓ.ም. ተወለዱ። ዙር አባ ዝማሬ ቤተልሔም ደግሞ ድጓ በእጃቸው ጽፈውና አመ\ክተው በሁለቱም በመምህርነት ተመርቀዋል። ከ1941ዓ.ም. ጀምሮ ለ60 ዓመታት ከፊደል እስከ ጾመ ድጓ፣ ከዝማሬ እስከ ድጓ በታላቅ ትጋት በማስተማር ስመ ጥር ሊቃውንትን አስገኝተዋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንንም በሙሉ ኃይልና ፍላጎት በማገልገል ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ይኖራሉ።

በተጨማሪም ብራና እለስልሰው፣ ብዕር ቀርጸውና ጥቁርና ቀይ ቀለም አዘጋጅተው 2ምዕራፍ፣ 1አባጃሌ ዚቅ፣ 2ጾመ ድጓ፣ 12ዝማሬመዋሥዕት፣ 3ድጓ፣ 4የዓመት ስንክሳርና 18ተእምር፣ ገድልና ድርሳን በብራና ጽፈው ለአገልግሎት አስራጭተዋል።

እግዚአብሔርም ሀብተ ክህነትን፣ ሀብተ ሥጋንና የዕድሜን ጸጋ አድሏቸዋል። አሁንም በሥጋና በትምህርት ከወለዷቸው ልጆቻቸው የልጅ ልጅ ዐይተው፣ ከምንኩስና ማዕረግ ደርሰው፣ ማስተማራቸውን እንደቀጠሉ ይገኛሉ። ስለሆነም የ90 ዓመቱን ባለግርማ ሞገስ አረጋዊ ሊቅ የኔታ ውባገኝ ባንቴን ባስታውሳቸው በደስታ ተውጬ ነው።

የቅል ውሃ አያከራምና ያም ያም ሊቀባበላት ወዲያው ተንጠፍጥፋ ታልቃለች። ጥሬ ቆርጥመናልና ውሃ ጥም ቅጥል ያደርገናል። ያን ጊዜ «እመይቴ ውሃ!» እያልን በዚያ ጨለማ ስናስከልክ «አፈወርቅ ነሽ! የት ነሽ!» እያሉ ከእርጎ የሚመረጠውን የገብስ ጠላ በጉቶ የሚያስቸብቡኝ ክብርት ባለቤታቸው እማሆይ ያጤነሽ ትርልኝም ከሀሳቤ ወጥተው አያውቁም።

www.debelo.org



መልአከ ሕይወት አባ ውባገኝ ባንቴና ደቀመዛሙርቶቻቸው



መልአከ ሕይወት አባ ውባገኝ ባንቴና
እማሆይ ያጤነሽ ኑርልኝ
አሁን በሚገኙበት የምንኩስና ማዕረግ



## «አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ . . . »

## እንዴት እንደ ተጻፈች

ግርማዊ ግእዝ «ዐፄ» ተብለው ለብዙ ሽህ ዓመታት መንግሥት መሥርተው ይኖሩ ነበር። በኋላ ግን «እንዳማሩ መሞት አይገኝም።» የተባለው ነገር ደረሰባቸው። በተለይ በነዐፄ አምደ ጽዮን፣ በነዐፄ ይስሐቅና በነዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከወታደሮች ጋር ልዩ ቅርበት የነበራቸው ሻለቃ አማርኛ ብርቱ ተፎካካሪያቸው ሆኑ።

«ሹመት በተርታ፣ ሥጋ በገበታ።» እንዲሉ ሻለቃ አማርኛ በአለቃ ዘነብ ኢትዮጵያዊ አቅራቢነት በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተቀብተው «ዐፄ» ሆኑ። ግእዝንም ከሥልጣነ መንግሥት አባረው ቤተ መንግሥቱን ከተቆጣጠሩት እነሆ ሽህ ዓመት ሊሞላቸው ነው።

ግእዝም ሻለቃ አማርኛን ፈርተው ቤተ ክርስቲያን ገብተው ደወሉ። ከዚያም በነየኔታ እጉብ፣ በነየኔታ መንክር፣ በነየኔታ ማእበል፣ በነየኔታ ግጨው፣. . አማላጅነት ከሞት ተርፈው አንዳንድ ተማሪዎች ብቻ እየተላላኳቸው እንደ ባሕታዊ ከሰው ተገልለው ኖሩ።

ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ በሻለቃ አማርኛ ላይ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ . . . የሚባሉ ዓለም አቀፍ ተፎካካሪዎች



www.debelo.org

መጥተውባቸዋል። ስለዚህም ጉዳይ ከአባቢያቸው ነገሥታት ሁሉ ጋር በመመካከር ላይ ናቸው። እናም እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ባህልና ሥርዓት እያሳደጉ ብርቱ ዓሰም ዓቀፍ ተወዳዳሪ ሰመሆን በጣም እየጣሩ ናቸው። ግእዝንም ቢሆን ልምዳቸውን እንዲያካፍሉና በብዙ ሽህ ዓመታት ያጠራቀሙትን ታሪክ፣ ባህልና ዕውቀት ለትውልዱ እንዲያስተላልፉ እያግባቧቸው ነው። እንዲያውም የራሳቸውን ትምህርት ቤት አቋቁመው ደቀመዛሙርቶቻቸውን እንዲያሠለጥኑ በጀት እስከ መመደብ ደርሰዋል።

እነሆ ግእዝ በዚህ ዕድል ተበረታተው ጠቃሚ አገልግሎታቸውን ማበርከት ጀምረዋል። ስገዳም በደብር፣ በዋሻ በመንደር፣ በዕቃ ቤት በቤተ መዘክር፣ ያስቀመጡትን ታሪክና ዕውቀት እየገሰጹ ነው።

አሁንም ከደቀመዛሙርቶቻቸው እግር ሥር ሆና በግማሽ ልቡ የሚያስተምሩትን ያዳምጥ የነበረውን ዘንበሪጡ ኩተኛበት ቀስቅሰው ይህችን «እንጋሪ ምሳሌ ዘግእዝ - የግእዝ ምሳሌያዊ እነጋገሮች»ን በቃላቸው እየነገሩ አጻፉ። የቀረውንም ሌላ ጊዜ ሊያወጉት ቃል ገብተው የጸሎት ለዓት ስለደረሰባቸው በራቸውን መሰለ አድርገው ማጉተምተም ያዙ። በራቸውን ከፍተው ለስብከት እስኪወጡ ከእውደ ምሕረቱ ተሰባስበን ይህችን እየቀጸልን እንጠብቃቸው።



www.debelo.org

# ማውጫ


| እርእስት | ገጸት |
| --- | --- |
| ምስጋና | ፩ |
| ማስታወሻ | ፫ |
| «እንጋሪ. . . » እንዴት እንደ ተጻፈች | ፭ |
| መቅድም | ፯ |
| መግቢያ | ፲፩ |
| ምሳሌያዊ እነጋገሮች | 1 |
| ምርቃት | 87 |
| የቃላት መፍቻ | 89 |
| ዋቢ መጻሕፍት | 90 |

# መቅድም

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሥነ ቃል ዘሮች ናቸው። በጽሑፍም ሆነ በንግግር፣ በወግና በጨዋታ ጊዜ ይጠቀሳሉ። የተጠቀሱበትን ጉዳይና የመጡበትን አውድ በአጭሩ ያስረዳሉ። ምስሌያዊ እንጋገሮች የተፈጠሩት ከእውነተኛ ነገር በመሆኑ ያንን የተመሠረቱበትን ዝርዝር ገጠመኝ አጠቃሰው ቅልብጭ አድርገው ይዘው የሚገኙ ብቻ አይደሉም። አሁን ለሚጠቀሱበት ተመሳሳይ ጉዳይም ሁነኛ አስረጅና ፍቱን መግለጫም ይሆናሉ እንጂ።

ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደ ተረት፣ ግጥም፣ ቅኔ፣ ልበሰድ፣ . . . ራሳቸውን ችለው አይነገሩም። እነሱ የሚጠቀሱት አሁን የተያዘውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት፣ ለማጉላትና ብሩህ አድርጎ ለማሳየት ነው። እግረ መንገዳቸውንም የየዘመኑን ኅብረተሰብ ባህል፣ ማኅበራዊ ተራክቦ፣ ፖለቲካና እምነት ይገልጻሉ። ይህንንም ብርሃኑ(1992) እንዲህ ብለው ገልጸውታል።

> *በረጅም ዐ/ነገሮች እና ንግግሮች የሚብራሩትን ሀሳቦች በአጭሩ የመግለጽ ኃይል ያላቸው የስነ ቃል ዘርፍ የሆኑት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የትውልድ አሻራዎችና የማንነት መግለጫዎች ናቸው። ምሳሌዎችን በመመርመር በዘመኑ የነበሩትን ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አመለካከቶች መገንዘብ ይቻላል። ምሳሌዎች ለንግግርና ለጽሑፍ ለዛና ጣእምን የሚሰጡ ቅመሞች ናቸው። የአንድን ሰው የቋንቋ ችሎታና እውቀትንም ለመለካት እንደ መስፈርት ሆነው ያገለግላሉ።*

ሰዎች በውል የተገነዘቡትንና በማኅበራዊ ህይወታቸው ያጋጠማቸውን ነገር እጥር ምጥን፣ ስብስብ ክውን አድርገው ዜማና ምጣኔ ባለው ሐረግ፣ ዐረፍተ ነገር ወይም በባለ ሁለት ስንኝ ግጥም መልክ በየቋንቋቸው ያስቀምጡታል። ይህም ለሌላ ጊዜ የሚጠቀስ ምሳሌያዊ እነጋገር ይሆናል። ሌላ ተመሳሳይና ተቀራራቢ ክንዋኔ በሚያጋጥም ጊዜ ተጠቃሽ ሆኖ ሲመጣም «. . . ይበል እገሌ! . . . ይበሉ!» እያሰኘ አንገት ያስነቀንቃል፤ የነገር ማስረገጫና መቋጫ ይሆናል። ለምሳሌ እርጎ እየጠጣ ያለ ሰው እርጎው እንጀቱን ቢያርሰው እርካታውን ሁሉ በዝርዝር ለመግለጽ ይቸገራል። ሀሳቡ ሲተረማመስበትም «ኧረ ዲያ ‹የሥጋ መድኃኒት ሳም፣ የነፍስ መድኃኒት



www.debelo.org

ማርያም› ይበሉ!» ብሉ በአጭሩ ሲገላገል ይችላል።

ምናልባት የዓለም ሕዝቦች ቋንቋዎች ሁሉ በዚህ ዓይነት እጥር ምጥን ተደርገው ተከሽነው የተቀመጡ ምሳሌያዊ እነጋገሮች ይኖሯቸው ይሆናል። የሀገራችን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችም በምሳሌያዊ እነጋገሮች የበለጸጉ ናቸው። የሁሉንም ባይሆንም የተወሰኑትን በአንዳንድ ጽሑፎችና በተለይም በእጩ ተመራቂ ተማሪዎች የጥናት ወረቀቶች ውስጥ መመልከት ይቻላል።

ከሀገራችን ቀደምት ቋንቋዎች አንዱ የሆነው ግእዝ ጥንታዊ የንግግርና የጽሑፍ ቋንቋ መሆኑ ቢታወቅም ብዙ አልተጠናም። ይሁን እንጅ በሁሉም የሥነ ቃል ዓይነቶች የተከማቸ ጥበብና የተራቀቀ ፍልስፍና አለው። ከነዚህም ውስጥ የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይገኙበታል።

የምሳሌያዊ አነጋገሮች ሁሉ መነሻቸው ተረት፣ ገጠመኝ ወይም ታሪክ ነው። ብዙ ጊዜ ተናጋሪያቸው ወይም ፈልሳፊያቸውም አይታወቅም። አልፎ አልፎ ታዋቂ ሰዎች የተናገሯቸው አባባሎች ሲኖሩም ስም እየተጠራ «እገሌ እንዲህ አለ።» ቢባልም ቁጥራቸው



አነስተኛ ነው። የግእዝ ምሳሌያዊ እነጋገሮችም ይህን ሀቅ ያረጋግጣሉ። በየቦታው ተደጋግመው የሚነገሩትንና በተለያዩ የታሪክና የቅኔ መጻሕፍት የተመዘገቡትን ትረካዎች መሠረት በማድረግ ሦስት ምሳሌዎችን እንመልከት

*፩ኛ ዚአከ ለዚአየ፤ ዚአየ ለዚአከ።*

እንድ ንጉሥ ገንፎ የመብላት ፈተና አዘጋጀ። ገንፎውን መብላት የሚቻለው ሁለት ሆኖ ነበር። ለመመገቢያነት የተሰጡት የእንጨት ማንኪያዎችም በጣም ረጃጅሞች ነበሩ። መጨበጥ የሚቻለው ደግሞ ከማንኪያዎቹ እጀታ ጫፍ ላይ ብቻ እንደሆነ ለተወዳዳሪዎች መመሪያ ተሰጠ።

የንጉሡ ወታደሮች፣ ተከታዮችና መማክርቱ ሳይቀሩ ገንፎውን በልተው ለመሸለም ሲሉ ሁለት ሁለት እየሆኑ እየቀረቡ ተወዳደሩ። ይሁን እንጅ ረዣዥሞቹ ማንኪያዎች በየተወዳዳሪዎቹ ጆሮ ግንዶች እያለፉ መመገብ ሳይችሉ ቀሩ። በመጨረሻ ሁለት የቅኔ ተማሪዎች ቀርበው *ዚአከ ለዚአየ፤ ዚአየ ለዚከ - አንተ ለኔ፤ እኔ ላንተ።* በመባባል ማዶ ለማዶ ተቀምጠው



www.debelo.org

እየተጎራረሱ ሙጥጥ አድርገው በልተው ሽልማታቸውን ከንጉሡ እንደተቀበሉ ይተረካል፡፡ድርጊቱ አንድ ቀን የተከናወነ ቢሆንም ብሂሉ ግን እስካሁን ይሠራበታል፡፡

*፪ኛ ለዘመጽአ በሰላም በዝ አባርከ፤ ወለዘመጽአ በኀኬት በዝ አዘተርከ - በሰላም የመጣውን በዚህ እባርከዋለሁ፤ በክፋት የመጣውን በዚህ እዘተርከዋለሁ፡፡*

አንድ ባህታዊ ከአናቱ የመስቀል ቅርጽ ከታች ደግሞ እንደ ጦር የተሳለ ጫፍ ያለውን የብረት ዘንግ ይዘው በበረሃ ይጓዛሉ፡፡ አንድ ሌላ ሰው ያገኛቸውና «አባቴ የያዙት ብረት ዘንግ ከላይ መስቀል ከታች ጦር አለው፡፡ ለምንድነው?» ቢላቸው ባህታዊዉ «ይህን የያዝኩት ለሁለት ነገር ነው፡፡ አንደኛ በዚህ ጭው ባለ በረሃ እንደ እርስዎ ያለ ሰላማዊ ሰው በሰላም ከመጣልኝ በላይኛው በመስቀሉ እባርከዋለሁ፡፡ ሁለተኛም እንደ ወንበዴ በክፋት ከመጣብኝ ግን በታችኛው በሹሉ አንጀቱን እዘረግፈዋለሁ» እንዳሉት ይነገራል፡፡

የባህታዊዉ ብሂል «ጅብ ከሚበላህ በልተኸው ተቀደስ» ወይም «ሕወይ የኔ ኑሮ እንዲያው ተሰባብሶ፤ መስቀል ተሰላጢን ህዘንና ለቅሶ፡፡» ሳያሰኝ አይቀርም፡፡



www.debelo.org

*፫ኛ ክልዔሆሙ ኀቡረ ተከዙ*

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ቀይ ባሕርን ተሻግረው የመንንና ሌሎችንም የዐረብ ህገራት ይገዙና ያስተዳድሩ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን የነበረ ንጉሥ ከባሕር ማዶ ዘመቻ ሲመለስ «ከዚህ አፈር ያዙ!» ብሎ ሰራዊቱን አዘዘ፡፡ ይህን ጊዜ ግማሹ «በረሃ ለበረሃ የተንከራተትነው አንሶ ‹አፈር ተሸከሙ› እንባል!» በማለት ምንም ሳይዝ ቀረ፡፡ እኩሉ ግን «ምንም ቢሆን የንጉሥ ትእዛዝ ነው! ‹የንጉሥ ትእዛዝ አነሰ ብለው አይጨምሩ፤ በዛ ብለው አይቀንሱ፡፡› እንይዛለን፡፡» በማለት ትንሽ ትንሽ አፈር በየጨርቁ ጫፍ ቋጠረ፡፡

ከቀናት በኋላ ባሕሩን ተሻግረው የኢትዮጵያን መሬት ሲረግጡ ንጉሡ «የያዛችሁትን አፈር አውጡ!» ባላቸው ጊዜ የቋጠሩት አፈር ወርቅ ሆኖ ተገኘ፡፡ በዚህም ምክንያት ማንም ደስተኛ ሊሆን አልቻለም፡፡ ሁለቱም ወገኖች እኩል አዝነዋል፡፡ የያዙት «ለአፈር ብንጨምበት ምን ነበር!» ያልያዙትም «ምነው የእነሱን ያህል እንኳን በያዝን!» እያሉ ተብሰልሰልጭተዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚ መነሻነት እንዲህ ሲባል ይኖራል፡፡

*ዘአንዘ ወርቀ ወዘኢአንዘ፣*

*ክልኤሆሙ ንቡረ ተከዙ።*

ወርቅ የያዙትም ያልያዙትም

ሁለቱም በአንድነት አዘኑ።

የአማርኛው «የዘገነም አዘነ፣ ያልዘገነም አዘነ።» የሚለው ምስሌያዊ አነጋገርም መነሻው ይህ መሆኑ አይጠረጠርም።

ይህ ትረካ የማይታመን ሊመስል ይችል ይሆናል። ነገር ግን የነዐፄ ካሌብን፣ የነዐፄ ላሊበላን፣ የነዐፄ ዮሐንስ ፩ኛን ወዘተርፈ ታሪክና ገድል መመልከት እንዲህ ያለውን ጥርጣሬ ያስወግዳል። ነገሥታቱ ሃይማኖተ ጽኑዎች፣ ሥጋዊ ጥቅምና ኑሮ የማያታልላቸው መናኞች ነበሩ። ይህንም ከሚከተሉት ታሪኮች በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።

ዐፄ ካሌብ የመን ዘምተው የተጨቆኑ ክርስቲያኖችን ከአይሁድና ከአረማውያን ነጻ አወጡ። ከዚያም በባዕድ ሀገር ድል ስለሰጣቸው በመደሰት «ምንተኑ እዐስዮ ለእግዚአብሔር - ለእግዚአብሔር ምን ላድርግለት? .»'ተክለ ጻድቅ(1966) እና ትንሣኤ(1993) በማለት



www.debelo.org

መንግሥታቸውን ትተው በጸሎትና በአምልኮተ እግዚአብሔር ተጠምደው አሥራ ሁለት ዓመት በብሕትውና ኑረው አርፈዋል። በዚህ ተግባራቸውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የቫቲካን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጻድቅነት ሲያከብሯቸው ይኖራሉ።

ሌላው «ጻድቁ ዮሐንስ» የሚል ቅዱስ ተግባራቸውን የሚገልጽ ስመ ሥርጋዌ የተሰጣቸው የዐፄ ዮሐንስ ፩ኛ ታሪክም ይህንኑ ያጠናክራል። ዐፄው በቤተ መንግስታቸው ግቢ ገንዳ አሰርተውና ውሃ አስሞልተው ከሚያስረቡት ዓሣ ተጠብሶ ለግብር ቀረበ። ምሳ እየተበላ ሳለ የተጠበሰውን ዓሣ አያዩ «እውነት ብንናገር እኮ ይህ ዓሣ ቁሞ ይሄድ ነበር።» አሉ ይህን ጊዜ ከአጠገባቸው የነበሩት ሁሉ የየልባቸውን ተናገሩ። ንጉሡም «እኔስ ይህችን ከንቱ ዓለም ንቄ አጥቅቼ በምናኔ ብኖር አወዳለሁ።» አሉ። በዚያች ቅጽበት ለምሳ ተጠብሶ ቀርቦ የነበረው ዓሣ ወደተያዘበት ሰው ሠራሽ ባሕር ዘሎ ገባ አድማሱ(1963)እና ተክለ ጻድቅ(1966)። ስለዚህ ሁኔታም በወቅቱ የተደረሰው ይህ አነጻጻሪ ቅኔ በደንብ ያስረዳል።

ሥላሴ

እእዳው እስ ጴጥሮስ እም ክልዔ ዓሣት ወእም ኀምስቱ
እስፈሬዳተ ፍት ዐሥረ ወክልዔ
እምድኅረ ተረፉ እግኅሣ፤
ኢየሱስ እመ እጽገበሙ ሰዘምእት ኀምሳ።
ሰመንኖስ ዓሰመ እመ ዮሐንስ ኀሠሣ፤
እእዳዊሁ ቅድመ ይግሥሣ፤
ድኅረ ሞት መልዓ ሰባሕር እስከነ ከርሣ፤
በፈቃዱ ዘተግኅሠ ዓሣ።

ትርጉም

ኢየሱስ ሁለቱን ዓሣዎችና
አምስቱን እንጀራዎች አበርክቶ፤
አምስት ሽዉን ሰዎች ባጠገባቸው ጊዜ፤
የነ ቅዱስ ጴጥሮስ እጆች፤
የተራረፈውን እሥራ ሁለት ሞሰብ ፍርፋሪ እነሱ።
በእንጻሩ ዮሐንስ ዓለምን ንቆ ሰመመነን በሻ ጊዜ፤
እጆቹ ሳይነኩት በፈቃዱ የተነሳ ዓሣ፤
ከሞት ተነስቶ ባሕርን እስክ እፍ ጢሟ ሞላት።



www.debelo.org

ምስጢር

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ዓሣዎችንና አምስት እንጀራዎችን አበርክቶ አምስት ሽህ ሰዎችን ማጥገቡና የተረፈውንም እሥራ ሁለት ሞሰብ ቁርስራሽ ደቀ መዛሙርቱ መሰብሰባቸው ተጽፏል (ሉቃ9÷12-17)። እንዲሁም ዐፄ ዮሐንስ የበቁ መንፈሳዊ ሰመሆናቸው የተነሳ ዓለምን ንቀው መመነን በማሰባቸው የተጠበሰው ዓሣ ከሞተ በኋላ ህያው ሆኖ ወደ ባሕሩ ተመሰሰ ይላል የቅኔው ምሥጢር።

ህዝቡም በጊዜው እንዲህ ብሉ ገጥሞላቸዋል።

«የደጉ ዮሐንስ ደግነት ቢነሳ፤
ዘሉ እባሕር ገባ የተጠበሰ ዓሣ።»

ልጆቿ የሞቱባት በዘመናቸው የነበረች ሴት ደግሞ

«ልጆቼ አልቀውብኝ ትንሹ ትልቁ፤
የልጆቼን ማለቅ ንጉሥ ቢጠይቁ፤
ከሞቱ በኋላ ልጆቼ ካሰቁ፤
ያስነሱልኝ ነበር ዮሐንስ ጻድቁ።» ብላ የሰቅሶ ግጥም ደርድራለች።

«አፈር ወርቅ አይሆንም።» የሚል ወገን ቢኖር ደግሞ

የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች መጽሐፍ ቅዱስ ተኮርና ከሃይማኖት ጋር ተያያዥ መሆናቸውን ማጤን ያሻዋል። መጽሐፍ ቅዱስ «ለዘየአምን ኵሉ ይትከሃል! - ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።» ይላልና።

እንዲህም ስለተባለ «የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስና ሃይማኖት ተኮር ብቻ ናቸው።» ብሎ ወርውሮ መጣል ፍጹም አይቻልም። ግእዝን የቅርስ ባለቤትና ጠባቂዋ የኢተዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ይዛው ትገኝ እንጅ የሁሉም ዜጎች ሀብት ነው። የሀገሪቱ ብሔራዊ የንግግርና የጽሑፍ ቋንቋ ስለነበር ፍጹም ሰብአዊና ማኅበራዊ አባባሎች ሞልተውታል። ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት።

*አኮ በሲበት አላ በአእምሮ*
በሽበት አይደለም፣ በማስተዋል ነው እንጅ።
አድሮ ቃሪያ።

*መጥመኒ እመጥወከ*
ስጠኝ,እሰጥሀለሁ።
እከክልኝ ልክክልህ።

*ምጢት የሐውር ኀበ ምጢት*
ሙት ወደ ሙት ይሄዳል።
ተመሳሳይ ክንፍ ያላቸው ወፎች፣
በአንድነት ይበራሉ።

*ወለእመ ሖርከ ብሔረ ባዕድ ኩን ከማሆሙ*
ሌላ አገር ብትሔድ፣ እንደነሱው ሁን።
እንደ ንጉሡ፣ ያጎንብሱ።
እንደ አገሩ ይኖሩ፤ እንደወንዙ ይሻገሩ።
እንደ አገሩ፣ ጅብ ይገሩ።

*ዘበልዐ በለቅም የጎድር በሰላም*
በልኩ የበላ፣ ሰላማዊ ዕንቅልፍ ይተኛል።
እህል ባሳደገ፣ ደመኛ ይሆናል።

የሚሉት ጥሩ ማሳያዎች ናቸው።

ከነዚህ ማሳያዎች ጋር የሚመደብ ሌላ የአንድ ያልታወቀ ፈላስፋ እንደሆነ የተነገረ ብሂልም አለ። ብሂሉ ከዘመናችን አስጨናቂ፣ አስቃቂና ትውልድ ጨራሽ በሽታ ከኤች አይ ቪ ኤድስ ጋር በተያያዘም ሊጠቀስ የሚችል ነው። እንዲህ ይላል።

*ዘዐቀበ እስኪቶ፣ የዐቅብ ሀይወቶ።* ኪዳነ ወልድ(1948)
ሀፍረተ ሥጋውን የጠበቀ፣ ህይወቱን ጠበቀ።


www.debelo.org

መጠንቀቅ፣ መጠበቅ።

ክርሴስ የተባለ ፈላስፋም ከዚህ ብሂል ጋር የሚስማማ ድርጊት ይፈጽም ነበር። መሽቶ ሲተኛ ቀኝ እጁን ከአቁግራ እጁን ደግሞ ከብልቱ ላይ ጭኖ ያነጋ ነበር። እንዲህ ማድረጉም አፍና ብልት በአግባቡ ካልተያዙ እዳ ከታች ችግር አምጪ መሆናቸውን ማስተማሩ እንደሆነ ሞገስ(1957) ገልጸዋል።ምናልባት ብሂሉም የዚህ ሰው ይሆን?

ማኅበራዊ ጉዳይ ከያዙት በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስና ሃይማኖት ተኮር የሆኑት ምሳሌያዊ አነጋገሮችም ለሃይማኖታዊ ተግባር ብቻ የሚጠቀሱ አይደሉም። በልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችና አጋጣሚዎች ሲጠቀሱና ሲጻፍባቸው የተስተዋሉና የሚስተዋሉ ናቸው። ለምሳሌ ያህል «ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ነቢይ በሀገሩ አይከበርም።»(ሉቃ4÷24) የሚለውን ብንመለከት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው በቅዱስ ወንጌሉ የተጻፈ ዐረፍተ ነገር ነው። ነገር ግን በዕውቀቱ(1995) ከዚህ ተነስተው የሚከተለውን ግጥም አስነብበውናል።

*ትናንት*

*«ነብይ ባገሩ አይከበርም»*

*ዛሬ*

*ነብይ ባገሩ አይኖርም*

*ነገ*

*ነብይ ባገሩ አይፈጠርም።*

ከዚህም ሌላ አንድ የተማረ አዋቂና ባለሙያ ሰው ተገቢውን ቦታና ክብር ባጣ ጊዜ ሁሉ ራሱ ሰውየው ወይም ተመልካቹ ሊጠቅሰው ይችላል። «ለምን የጌታን ቃል ካለቦታው ጠቀስክ?» ሲባል አይችልም። «አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው።» አእምሮ(1965) እንደተባለው ሃሳብ፣ ገጠመኝ፣ ቋንቋ፣ ሥነ ቃል፣ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ . . . ሁሉ የጋራ ናቸውና።

አ. ታ.



www.debelo.org

# መግቢያ

እዚህ የቀረቡት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ግእዝ አዋቂዎች ለነገር ማስረገጫና ለጫወታ ማሳዘቢያ ሲናገሩ በመስማት የሰበሰብኳቸው ናቸው። ሊታወሱ የሚችሉት በንግግር አጋጣሚ በመሆኑ ሊጠቀሱ የሚችሉበትን አጋጣሚ በፍላጎት መፍጠር አይቻልም። ይሁን እንጅ ለአንዳንድ የግእዝ ወዳጆች በየአጋጣሚው በማስታወሻ የያዝኳቸውን ምሳሌያዊ አነጋገሮች እያነበብኩላቸው ትዝ ያሉቸውን እየነገሩኝ ቁጥራቸውን ለማበርከት ሞክሬአለሁ።

በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝ አንድ የሥነ ቃል ዓይነት በመጀመሪያ ሙከራ በአጥጋቢ ሁኔታ ሊሰበሰብ አይችልም። እናም ቁጥራቸው ባይበዛ አያስገርምም። ወደፊት እኔም ሆንኩ ሌሎች በነዚህ ላይ ልንጨምርባቸው እንችላለን የሚል ተስፋ አለኝ።

ምሰሌያዊ አነጋገሮቹ የተገኙትና የተወሰዱት ከብሉያትና ከሀዲሳት (መጽሐፍ ቅዱስ)፣ ከመጻሕፍተ መነኮሳትና ከመጻሕፍተ ሊቃውንት እንዲሁም ከአበውና ከፈላሰፎች ንግግሮች ነው። ነገር ግን እዚህ በጽሑፍ የቀረቡትም ሆነ የአማርኛ ፍች የተሰጣቸውና እቻ



www.debelo.org

ምሰሌያዊ ንግግር የተቀመጠላቸው በምሰሌያዊ አነጋገርነታቸው በሚሰጡት አገልግሎት ብቻ ነው። በየመጻሕፍቱ ውስጥ በሚገኙበት አውድ (አገባብ) አይደለም። በመሆኑም አገባብ ሲገደፍ ወይም ቃል ሊዘዋወር ይችላል።

ለማንኛውም አንባቢ ቅቡል እንዲሆን ሲባልም የአንድ ምሳሌያዊ አነጋገር ፍች በሦስት ተደጋጋፊና ተከታታይ ደረጃዎች ቀርቧል። የፍችዎቹ ደረጃዎችም፣

፩ በቀጥታ ወደ አማርኛ በመተርጎም፣

፪ ይበልጥ ለማብራራትና ግልጽ ለማድረግ እቻ የአማርኛ ምሰሌያዊ አነጋገሮችንና የታወቁ ጠቢባን የተናገሯቸውን ምርጥ አባባሎች በማስቀመጥ፣

፫ ለአንዳንዶቹ ደግሞ «ለሆድ ህመም ብላበት፤ ለራስ ምታት ጨህበት።» በሚለው ዓይነት ፍቻቸውን ለማጉላትና በሌላኛው ገጽታ ለመስረዳት እቻ ግን ተቃራኒ ምሰሌያዊ አነጋገሮችን በማቅረብ ናቸው።

ለአንባቢና ለጠቃሽ እንዲመቹ በተለመደው በ«ሀ፣ለ፣ሐ፣መ፣ . . . » የፊደል ተራ ቅደም ተከተል ቀርበዋል። ምንም እንኳን ከየመጻሕፍቱ አንቀጾች የወጡና ከየሰዉ

አፍ የተሰበሰቡ ባይተዋሮች ቢመስሉም በራሳቸው ሙሉና የተስተካከሉ ናቸው። እጅግ የጠራና የነጠረ ሀሳብም ይዘዋል። ለማይን ያደመቁ ብሩሃን ከዋክብት፣ ምድርን ያስጌጡ የፈኩ አበባዎችና ከወይን ከማንጎ፣ ከሎሚ ከትርንጎ፣ . . . የተለቀሙ ብስልና ጣፋጭ ፍሬዎች ናቸው። እንዲሁም እያንዳንዳቸው ብቻቸውን ገላጭ፣ አዝናኝ፣ አስደሳች፣ አመራማሪና አፈላላፊ ስለሆኑ በጥሞና ቢስተዋሉ ደህና ነው። ግሩም ንባብ!

አፈወርቅ ታረቀኝ



www.debelo.org

## <u>አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ</u>

### ሀ

ሀቡ ዘነጋሢ ለነጋሢ፤ ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር።

የቄሳርን ለቄሳር፤

የእግኢአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ።

ሽማ በየፈረጁ።

ለውሽየ ያልኩትን ልጅ ቢበላብኝ አልወድም።

የአብዬን ለእምዬ። (ተታራኒ)

ሀብ ለኵሉ ለዘሰአለከ።

ለለመነህ ሁሉ ስጥ።

ልብስህን ለውሃ፣ ገንዘብህን ለደሃ።

የለበሱት ያልቃል፤ የሰጡት ያጸድቃል።

መስጠት ቤት አይፈታም።

ሀብ ፍኖተከ ለእግዚአብሔር።

መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ።

ሃይማኖት እንተ አልባቲ ምግባረ ሠናይ ምውት ይእቲ።

በጎ ሥራ ያልተሠራባት ሃይማኖት የሞተች ናት።

የወጥ ማጣፈጫው ጨውና ቅቤ፤

የሰው ማጣፈጫው ሃይማኖቱና ምግባሩ።

ጸሎት ያለፍቅር፣ ሃይማኖት ያለግብር፣ አይረባም።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ሃይማኖት ከግብር፣ ጸሎት ከፍቅር።

ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ።

በአባቶችሽ ፋንታ ልጆች ተተኩልሽ።

ሲፈጭ ሲጦካ፣ ሲወለድ ሲተካ።

### ለ

ለለእሐዱ በከመ ምግባሩ።

ለእያንዳንዱ እንደሥራው።

ሥራ ለሠሪው፣ እሾህ ላጣሪው።

ለልሳነ እጓለእመሕያውሰ አልቦ ዘይክል አግርሮታ።

እንደበቱን ሲገታ የሚችል የለም።

አፍ ነገር፣ ዐይን አገር አያጣም።

ምላስ ይተባል፣ ጥርስ ይወጋል።

ለሰሚዕ እጹብ።

ለሰሚው አስደናቂ።

ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል።

ለሰብእ ጸሩ ሰብአ ቤቱ።

የሰው ጠላቱ፣ ቤተሰቡ።

ጠላት ከውጭ አይመጣም።

ያገር ልጅ፣ የቂጥ እከክ።



www.debelo.org

## አንጋሬ ምሳሌ ዘግእዝ

ለስሒት መኑ ይሌብዋ።

ስህተትን ማን ያስተውላታል።

ነገር ሲያመልጥ፣ ራስ ሲመለጥ፣ አይታወቅም።

አንድ ቀን ቢስቁ፣ ዓመት ይጸጸቁ።

ለእመ ረከብከ ሰብአ በፍናት ኢትጻባእ፣

ወለእመ ተጻብአከ ኢታውስኦ።

በመንገድ ካገኘኸው ጋራ አትጣላ፣

እሱ ነገር ቢፈልግህም አትመልስለት።

እዚያው በጸበልህ።

በስምንተኛው ሺህ ባለው ተንካ ተንካ፣

እከክኛም ቢልህ ራሱን አትንካ።

ለእመ ብከ ሀብ ወለእመ አልብከ ኀሢ።

ካለህ ስጥ፣ ከሌለህ እዘን።

ምን ያምጣ ደሀ፣ ምን ያግሳ ውሃ።

ለእመ ብከ ጥበብ ጸሐፍ። ወልደ ሕይወት አንፍራንዝዊ

ዕውቀት ካለህ ጻፍ።

መንገድ ለማትረፍ፣ መማር ለመጻፍ።

ለወሀቤ ዝናም ማየ ከልእዎ።

ለዝናብ ጌታ ውሃ ነሱት።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

አበት ላም ይሰጣል፤ ልጅ አጓት ይነሳል።

ለውሂብ ኢትጕጕእ ወውሂበክ ኢትናፍቅ።

ለመስጠት አትቸኩል፤ ሰጥተህም አትጸጸት።

ሳይተርፈው ያበደረ ሳይቀበል ይሞታል።

ብዙ ቸርነት፣ ያመጣል ድህነት።

ለዘመጽአ በሰላም በዝ አባርኮ፣

ወለዘመጽአ በኀኬት በዝ አዘተርኮ።

በሰላም የመጣውን በዚህ አባርከዋለሁ፤

በክፋት የመጣውን በዚህ አዘተርከዋለሁ።

ያባሆይ መቋሚያ ላዩ ባላ፣ ታቹ ዱላ።

ለላምን ከፈለግህ፣ ለውጊያ ተዘጋጅ።

ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ፤ ወኢያወጽኦ አፍአ።

ወደኔ የመጣውን ወደ ውጭ አላወጣውም።

ከመጣሽ፣ ማርያም ታምጣሽ።

ለዘቦ ይሁብዎ፤ ወይዌስክዎ፤

ወለዘለ አልቦ እለሂ ቦ የሀይድዎ።

ላለው ይሰጡታል፤ ይጨምሩለታልም።

የሌለውን ግን ያለውንም እንኳን ይነጥቁታል።

የበላችው ያስታውካታል፣ በላይ በላዩ ያጎርሷታል።



## አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

ትናንት ጠምክን ያደርክ ማነህ? እኔ፤

ዛሬም ድገም።

ሁለተኛ ግፌ፣ ጫንቃየን ተገርፌ፤ ልብሴን መገፈፌ።

ሰተባባሰው፣ ማጭድ አታውሰው።

የቀከፋ፣ ተደፋ።

ለዘኢይሰቲ ወይነ ምንት ውእቱ ሕይወቱ።

ወይን የማይጠጣ ሰው ምን ሕይወት አሰው?

ጠጅ ሰጨዋ ልጅ መጫወቻ፣ ሰባሰጌ መማቻ።

ለዘየአምን ኵሉ ይትከሃል።

ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።

ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች።

ጌታውን ያየ አሽከር፣ ይጥላል በትግል።

ለጠቢብሰ አሃቲ ቃል ትበቍእ።

ላስተዋይ ሰው አንድ ቃል ይበቃዋል።

ብዙ ቢያወጉ፣ ይዘነጉ፤ ብዙ ቢተቹ ይሰለቹ።

እምሳ ዳቦ ከመላስ፣ አንዷን መኮርሸም።

ልሳነ እጓለ እመሀያው ሐጽ ወኵናት።

የሰው አፍ እንደ ተሳለ ጦር ነው።

የሰው ምላስ፣ እንጨት ይሰብራል።

www.debelo.org

ጦር ከወጋው፣ ምላስ የወጋው።

ልደትለ በኵሉ ልደት ጸውኦኒ በካልእ ዕለት። የቄስ ተማሪ

የልደት ድግስ በሁሉም ነው፤ ሌላ ቀን ጥሩኝ።

በፋሲካ የገባች ገረድ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስላታል።

ሎቱ ስብሐት።

ምስጋና ለርሱ ይሁን።

የፈጣሪ ያለህ!

## ሐ

ሐለሙ ሕልመ ወአልቦ ዘረከቡ።

ሕልም አለሙ፤ ያገኙት ነገር ግን የለም።

ደሀ ማታ እስር ይጠምዳል፤ ጧት አንድ ያጣል።

ሐንካስ በአግረ ዕውር ሖረ፤ ዕውርኒ በዐይነ ሐንካስ ነጸረ፤

ወበክልዔሆሙ ወይንየ ተመዝበረ።

እንካሳ በዕውሩ እግር ሄደ፤

ዕውሩም በአንካሳው ዐይን አየ፤

በሁለቱም አታክልቴ ተመዘበረ።

ድር ቢያብር፣ አንበሳ ያስር።

ሁሉም ቢተባበር፣ የት ይደረስ ነበር!

ሑር እምድኅሬየ ሠይጣን።





ሠይጣን ከኋላየ ሂድ።

እኔን ለቀቅ፣ ሉሪህን ጠበቅ።

ሕሙማን ይፈቅድዎ ለዐቃቤ ሥራይ ወእኮ ጥዑያን።

ባለመድኃኒቱን በሽተኞች ይፈልጉታል፤

ጤነኞች አይሹትም።

ካልታረደ አይገኝ ስባቱ፤ ከልተናገረ አይገኝ ብልሀቱ።

አህያ የለኝ ከጅብ አልጣላም።

ሕማማ ለዐይን ርዕየተ ጸላኢ።

ያይን በሽታዋ፣ ጠላትን ማየቷ።

ሕንጻ ወውሉድ ያዐብዩ ስመ።

ግንብና (ሕንጻ) ልጅ፣ ስምን ያስጠራሉ።

በጎ ሥራ ከመቃብር በላይ ነው።

የወለደ መልኩ ተለወጠ እንጅ አልሞተም።

ወድቆ ይነሱ በእጅ፣ ዘገይቶ ይከብሩ በልጅ።

ሕያዋን ይስእሉ ለሙታን፤ ሙታን ይሰእሉ ለሕያዋን።

ያሉት ለሞቱት ይጸልያሉ፤

የሞቱት ያሉትን ያስባሉ።

ሕይወት ወሞት ውስተ እደ ልሳን።

ህይወትም ሞትም በአፍ ይመጣሉ።

www.debelo.org

በአፍ ይጠፉ፣ በለፈለፉ።

መ

መምህራነ ኮኑ በበደወሉ፣ ፊደላተ ዘኖለቀ ኮሉ።

ፊደል የቆጠሩ ሁሉ፣ በያካባቢው አስተማሪዎች ሆኑ።

በየወንዙ ህሌ።

ላይማሩ መተርጎም፣ ላይበጡ ማከም።

ላይገሉ ጎፈሬ፣ ላይማሩ መምሬ።

መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ።

ፊት አይቶ የማያዳላ መምርና መካሪ።

አካፉን አካፉ ማለት።

መሠረተ ሕይወት ማርያም

ወጥንተ መድኃኒት ዘእምቀዲሙ።

የሕይወት መሠረትና የድኅነት መገኛ ማርያም ናት።

የሥጋ መድኃኒት ላም፣ የነፍስ መድኃኒት ማርያም።

መስዋዕቱ ለእግዚአቢሔር መንፈስ የዋህ።

የእግዚአብሔር መስዋዕቱ ቅን መንፈስ ነው።

ከመቶ አምላ ዳዊት፣ የልብ ቅንነት።

መስገርትስ ተቀጥቀጠት ወንህነስ ድኅነ።

ወጥመድ ተሠበረች፤ እኛ ግን አመለጥን።



www.debelo.org



መኑ ከመ አምላከነ?

እንደ እግዚአብሕር ያላ ማን አለ?

እንደ እናት ፍቅር ንጹህ የለም።

መኑ ዘደመሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት?

ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?

አዮ ሌላ፣ ወዮ ሌላ።

ማሞ ሌላ፣ መታወቂያው ሌላ።

መኑ የአቍር እሳተ ውስተ ጎጽኑ?

እሳትን በጭኑ ማን ይሸከማል?

እሷን ቢያቃጥላት፣ ከልጇ ላይ ጣለች።

መንግሥት እንተ ትትናፈቅ በበይናቲሃ ኢተጸንእ፤

እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት አትጸናም።

አንች ሸሽ ባይ፣ እኔ ሸሽ ባይ፤

ከቶ ማንኛችን፣ ቤቱ ቤቱ ባይ።

ጥርስና ከናፍር፣ ሲደጋገፍ ያምር። (ተቃራኒ)

መዐር ኢይጥዕሞ ለአድግ።

ለአህያ ማር አይጥማትም።

መዓተ ንጉሥ ከመ መልአከ ሞት።

የንጉሥ ቁጣ፣ የመልአከ ሞት ያህል ያስፈራል።

የበላይ፣ ያደባይ።

ወደሽን ቆማጢት ንጉሥን ታከብሪ!

መጋቢ እንበለ ሲሳይ፣ ጸባቲ እንበለ ማይ።

ያለ ምግብ መጋቢ የለ ውሃ ዋናተኛ።

ሳትታመም ተፈወስ፤ ሳትረክስ ተቀደስ።

ዳቦ የለም እንጂ ወተት በነበረ፣

በሱ ማግ እያረግን፣ እንበላ ነበረ።

መጠኑ ለረድእ በከመ ሊቁ።

የተማሪ ደረጃው (ክብሩ) እንደ መምሩ ነው።

ልጅ ቢሮጥ አባቱን አይቀድምም።

መጥወኒ እመጥወከ።

ስጠኝ እሰጥሀለሁ።

እከክልኝ ልከክልህ።

ማኅቶቱ ለሥጋከ ዐይንከ ውእቱ።

የሥጋህ መብራት ዐይንህ ነው።

ሁሉም አካል ነው፤ ግን እንደ ዐይን አይሆንም።

«ከዐይኔ ወዲያ!» አለ ሌባ!

ማዕረሩ ብዙኀ ወገባሩ ህዳጥ።

መኸሩ ብዙ ሠራተኛው ጥቂት።





ማይ ብዙኅ ኢይክል አጥፍአታ ለፊቅር።

ብዙ ውሃ ፍቅርን አያጠፋትም።

ፍቅር ትመነምናለች እንጅ አትጠፋም።

ፍቅር አያረጅም።

እውነተኛ ፍቅር ዘላለማዊ ነው።

ምሉዕ በኵለሄ

በሁሉ የተሟላ።

እንከን የለሽ።

ምሕረተ እፈቅድ ወአኮ መስዋዕተ።

ምሕረትን እወዳለሁ፤ መስዋዕትን አይደለም።

ከፍትፍቱ፣ ፊቱ።

ፊት በላህ? ፍትፍት?

ምንት ብከ ዘኢነሳእከ እም ካልዕከ?

ከሰው ያልወሰድከው ምን አለህ?

የተውሶ፣ ይሄዳል ተመልሶ፤ ታጥቦ ተተኩሶ።

ምንዳቤያትለ ኢኮና ርትቃተ እምኔከ፤

አላ ይነቅአ እምታህተ እገሪከ።

ችግሮችህ ሩቆች አይደሉም፤

ከእንተው ከራስህ ይመነጫሉ እንጅ።



www.debelo.org

ደባ ራሱን፣ ስለት ድጉሡን።

ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ።

ለሚተገብራት፣ ምክር መልካም ናት።

ተማክረው የፈሉት አይሸትም።

ሞኝ ከመካሪው፣ ዕውር ከመሪው፣ ይጣላል። (ተቃራኒ)

ሞቱ ለኃጥእ ጸዋግ።

የኃጢአተኛ አሟሟት የከፋ ነው።

ከሞቱ፣ አሟሟቱ።

ሞታ ለነፍስ ርኂቅ እም እግዚብሔር።

የነፍስ ሞቷ፣ ከእግዚአብሔር መራቋ።

ዓሣ በባሕሩ፣ ዝንጀሮ በገደሉ።

ምውት የሐውር ኀበ ምውት።

ሙት፣ ወደ ሙት ይሄዳል።

ተመሳሳይ ክንፍ ያላቸው ወፎች፣ በአንድነት ይበራሉ

ዘመድ ከዘመዱ፣ አህያ ካመዱ።

ምኲራብ አነመት ፀምረ፤ ወቤተ ክርስቲያን ተአጽፈቶ።

ምኲራብ ግምጃ ፈተለች፤ ቤተክርስቲያን ለበሰችው።

ገብሬ ይሠራል፣ ኒኮላ ይበላል።

በጨው ደንደሰ፣ በርበሬ ተወደሰ።



www.debelo.org



## ሠ

ሠናይ ለብእሲ መቅበርቱ ለኢመ ኮነ በውስተ ርስቱ።

የሰው መቃብሩ፣ በአገሩ ቢሆን መልካም ነው።

በሬ ወደ አገሩ ይሰባል።

ሰው ባገሩ፣ ዓሣ በባሕሩ፣ አንበሳ በዱሩ።

ሠናይ ብእሲ ያወጽኣ ለሠናይት፣

እም ሠናይት መዝገበ ልቡ።

በጎ ሰው ከበጎ ልቡ በጎ ነገርን ያወጣል።

የማሽላ ዘር፣ ከነአገዳው ቸር።

ሠናይ እገሪሆሙ ለእለ ይዜንዉ ሠናየ ዜና።

መልካም ዜና የሚነግሩ አብሣሪዎች፣

እግሮቻቸው ያማሩ ናቸው።

መልካም ወሬ አጥንት ያለመልማል፣

መጥፎ ወሬ ልብ ያደክማል።

የተሳከ፣ አፉን ለከከ።

ለወሬ፣ የሰው ፍሬ። (ተቃራኒ)

ሣህል ወርትዕ ተራከባ፤ ጽድቅ ወሰላም ተሰዐማ።

ቅንነትና ይቅርታ ተገናኙ እውነትና ሰላም ተሰማሙ።

ብልህና ቅባት፣ ብርሃንና መብራት።

ማርያም ወረደች።

ሥርወ ለኵሉ እኩይ፣ አፍቅሮ ንዋይ።

የክፉ ተግባር ሁሉ ሥሩ የገንዘብ ፍቅር ነው።

ገንዘብ የጠፋበት፣ ብዙ ኃጢአት አለበት።

ገንዘብ ወዳጅ ፍቅር አያውቅም።

አህል ያለው ፈርዛዛ፣ ገንዘብ ያለው ቀበዝባዛ።

ከኪሱ ሳንቲም የሌለው መንገደኛ፣

ሽፍቶች ባሉበት ጫካ ይሸልላል (ያቅራራል)።

ሥጋ ትጌይሳ ለነፍስ፤ በከዊነ ማኅደር።

ማደሪያ በመሆኗ፣ ሥጋ ነፍስን ትጨቁናታለች።

ባለጌና ውሻ በቤቱ ይኮራል።

ብላና ባገሩ ወይራ ነው።

## ረ

ርቱዕ አበው ይዝግቡ ለውሉዶሙ፤

ወእኮ ውሉድ ለአዝማዲሆሙ።

ወላጆች ለልጆች እንጅ፣

ልጆች ለወላጆች ሀብት ሊያከማቹ አይችሉም።

ውሃ ሽቅብ አይፈስም።

ርኅቀተ ሀገር፣ ኢይክልአ ለፍቅር።





የሀገር ርቀት፣ ፍቅርን አያስቀራት።

ልብ ሳይርቅ፣ ዐይን ቢርቅ፣ አያራርቅ።

ካይን የራቀ፣ ከልብ የራቀ። (ተቃራኒ)

## ሰ

ሰላም ሰላም ለሰራቄ ቅኔ ናሁዳ፣

ዳር ዳሩን ኮርኵሞ፣ መሀሉን ሳይጎዳ።

ቀነጣጥቦ ለሚሰርቅ የቅኔ ሌባ ሰላም ይሁን፤

ሰብእ ቤቱ ይጻረሮ ለሰብእ።

ሰውን የገንዛ ቤተሰቡ ይቃወመዋል።

ጠላት ከውጭ አይመጣም።

ከአብሮ አደግህ አትሰደድ።

ሰብአሰ ገጸ ይሬኢ፤ ወእግዚአብሔርሰ ልበ ይሬኢ።

ሰው ፊትን እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል።

ውስጡን ለቁስ።

ሰብእ አልብየ።

ሰው የለኝም።

የሌለው መዳኛም የለው።

ጨው የሌለው ምግብና

ሰው የሌለው ሰው አንድ ነው።

www.debelo.org

ሰብእ ወጣኒ፣ እግዚአብሔር ፈጻሚ።

ሰው ይጀምራል፣ እግዚአብሔር ይፈጽማል።

ሰው ያሰባል፤ እግዜር ይፈጽማል።

ሰው ይጨነቃል፤ የሚሆነውን አምላክ ያውቃል።

ሰብእ ይሠምር በዘይኄይሶ ሰሥጋሁ።

ሰው ሰሥጋው የሚጠቅመውን ይወዳል።

ከራስ በላይ ንፋስ።

ሰብእ ይቄድሶ ሰመካን፤ መካን ይቄድሶ ለሰብእ።

ሰው ቦታን ያስከብረዋል፤ ቦታም ሰውን ያስከብረዋል።

ከገጠር መሪጌታ የደብር ዐቃቢት።

የትም ተወሰድ፣ አዲስ አበባ፣ ሐረር፣ . . . እደግ።

ሰብእ ይከብር በእንተ ልብሱ።

ሰው በልብሱ ይከበራል።

ልብሴን ኖር በሰው።

ስንበት ተዐቢ እምኵሉ ዕለት፤

ወሰብእ ይከብር እም ኵሉ ፍጥረት።

ሰንበት ከዕለታት፣

ሰው ከፍጥረታት፣ ሁሉ ይበልጣሉ።

ከሰው መልካም ገበሬ፣ ከእህል መልካም ጥሬ።



www.debelo.org



ከሰው መርጦ ለሹመት፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት።

ሰእሉ ወይትወሀበክሙ፤ ኅሡ ወትረክቡ፤

ጕድጕዱ ወያርህዉ ለክሙ።

ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤

አንኳኩ ይከፈትላችኋል።

የለመነ ያገኛል፤ የነገደ ያተርፋል።

ከመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል።

ያልተገላበጠ ያራል።

ሰይፍ ዘክልዔ አፉሁ።

ሁለት አፍ፣ ያለው ሠይፍ።

አራት ዐይና።

በቀኝም ቀጥ፣ በግራም ቀጥ።

ሲሲታ ለነፍስ ቃለ እግዚአብሔር።

የነፍስ ምግቧ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ለነፍስህ ገዳም አሰልህ።

ስማዕ ወልድየ ሕገገ አቡከ።

ልጄ ሆይ! ያባትህን ትእዛዝ ስማ።

አባት ያበጀው፣ ሰልጅ ይበጀው።

ሰብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!

ሰአብ፣ ሰወልድና ሰመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፡፡

የሥላሴ ያለህ!

ስብሐት ለእግዚአብሔር!

እግዚአብሔር ይመስገን!

አንድዬን አይክፋው፡፡

ስብዓ ይወድቅ ጻድቅ ወይትነሣእ፡፡

ጻድቅ ሰባት ጊዜ ቢወድቅ ሰባት ጊዜ ይነሣል፡፡

ሰታይ ወአንስት ያስሕታሆሙ ሰመምህራን፡፡

መጠጥና ሴቶች መምህራንን ያስቷቸዋል፡፡

ሶበ ተሐውር ምስሰ ዕድውከ ኀበ መልአክ

ተዐረቅ በፍኖት፡፡

ወደ ዳኛ በምትሄድበት ጊዜ፣

በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ታረቅ፡፡

ነገርን በእርቅ፣ ወይፈንን በድርቅ፡፡

እርቅ፣ የሰው ደም ያደርቅ፡፡

ከተሟጋች ታራቂ፣ ካጣቢ አድራቂ፡፡

ሶበ ትረክቦ ኃጢአቱ ይጸልኣ፡፡

ጥፋቱን ሲያውቃት ይሰቀቃታል፡፡

ሲሰቁት ሜዳሙሉ፣ ሲይዙት ጭብጥ ሙሉ፡፡



www.debelo.org



ሶበ ኢያሥራሕክምዋ ሰእጐልትየ

እም ኢረከብክምዋ ሰአምሳልየ፡፡

በጥጃዬ ባላረሳችሁ፣ የእንቈቅልሼን ፍች ባላወቃችሁ፡፡

ቀ

ቀዳሚሃ ሰጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር፡፡

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡

የጥበብ መጨረሻ ፍቅር ነው፡፡ ኅሩይ ወ/ ሥላሴ

ቀዳሜ ሕይወቱ ሰሰብእ እክል ወማይ፣ ወይን ወሥርናይ

እህልና ውሃ ወይንና ሰንዴ

ሰሰው ሕይወት፣ መሠረት ናቸው፡፡

ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል፡፡

ቀጥቅጥ መዝራዕቶ ሰኃጥእ ወሰእኩይ፡፡

ክፉና ተንኮለኛን ሰው ድቅቅ ሰብርብር ማድረግ ነው፡፡

ባሰጌን ካላደገ፣ ያነቀ ጸደቀ፡፡

የባሰጌን ጠበቃ፣ አብረህ ውቃ፡፡

በፈሊጥ ክልገባው በፍልጥ!

ቃሰ መዋቲ ጽንዕት ይእቲ፡፡

የሙት ቃል አይሻርም፡፡

የሞተ አይወቀስ፣ የፈሰሰ አይታፈስ፡፡

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ሙትን መውቀስ፣ ድንጋይ መንከስ።

ቅኑተ ይኩን ኅቌክሙ ወኅትወ መኅትዊክሙ።

ትጥቃችሁ የጠበቀ መብራታችሁ የበራ ይሁን።

ቅኑት እንደ ገበሬ፣ ጽሙድ እንደ በሬ።

ቅድመ አውጽእ ሠርዌ እም ዐይንከ።

በመጀመሪያ ባንተ ዐይን ያለውን ግንድ አውጣ።

ጅብ በማይታወቅበት ሀገር ሄዶ

ቁርበት አንጥፉልኝ አለ።

ስማያውቁሽ ታጠኚ።

ቅድመ ይባኡ ውስተ ኅርየት

ይምሃርዎሙ ቃለ ሃይማኖት።

ከመሾማቸው በፊት

የሃይማኖትን ቃል ያስተምሯቸው።

ከመጠምጠም፣ መማር ይቅደም።

### በ

በስሐቅ ወበስላቅ ይበውእ ጸላኤ ሠናያት።

ክፉ መንፈስ በሳቅ በስላቅ ይገባል።

ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው።

በሳምናዊት ዘመን ትሴኰስ ፍቅር።



www.debelo.org

## እንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

በስምንተኛው ሺህ ፍቅር ትቀዘቅዛለች።

ስምንተኛው ሺ፣ ሰው አበላሺ።

የዚህ ዓለም ፍቅር ስኖ አዲስ፣

ማከስኞ ልብስ፣ ረቡዕ ብጥስጥስ።

በስምዐ ክልዔቱ ወሠለስቱ ይቀውም ኵሉ ነገር።

ነገር ሁሉ በሁለትና በሦስት ምሥክሮች ይጸናል።

ካንድ ብርቱ፣ ሁለት መዳኒቱ።

አንድ አይነድ፣ አንድ አይፈርድ።

በቀዳሚ ጕየይ፤ ወበካልዕ ጕየይ፤

ወበሳልስ ተንሥእ ወተቃተል።

በመጀመሪያውና በሁለተኛው ሽሽ፤

በሶስተኛው ግን ተነስተህ ተፋለም።

ሲበዛ ማርም ይመራል።

በብዙኅ ጻማ ሀለወነ ንባእ

ውስተ መንግሥተ እግዚአብሔር።

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት፣

በብዙ ድካም እንገባለን።

ያለ ድካም ዋጋ፣ ያለ መከራ ጸጋ አይገኝም።

በትዕግስትክሙ ታጠርይዋ ለነፍስክሙ።

## የ ግ እ ዝ ም ሳ ሌ ያ ዊ አ ነ ጋ ገ ሮ ች

በመታገሳችሁ ነፍሳችሁን ታድናላችሁ።

ትዕግስት ፍሬዋ ጣፋጭ ነው።

የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል።

ቀስ በቀስ ዕንቁላል በእግሩ ይሄዳል።

ሮም ባንድ ቀን አልተገነባችም።

በአርምሞ ይመስል ጠቢብ።

ዝም በማለቱ ብልህ ይመስላል።

ካልተናገረ አይገኝ ብልሃቱ፤ ካልታረደ አይገኝ ስባቱ።

በአይቴ ኀሊፊኪ ድኅ ተምኂረኪ?

በየት አልፈሽ ድኅ ተማርሽ?

የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል።

ወጡ ሳይወጠወጥ፣ ወስከንቢያው ቁጢጥ።

በከንቱ ዘነሳእክሙ ሀቡ በከንቱ።

ያስ ዋጋ የተቀበላችሁትን ያስ ዋጋ ስጡ።

ለሀገሬ ምን አደረግሁላት እንጅ፤

ሀገሬ ምን አደረገችልኝ አትበል።

በዘሠፈርክሙ ሎሙ ይሠፍሩ ለክሙ።

በሰጣችኋቸው ልክ ይሰጧችኋል።

በሠፈሩት ቁና መሠፈር አይቀርም።



## አ ገ ጋ ረ ም ሳ ሌ ዘ ግ እ ዝ

ብድር በምድር።

በዝ ግብርኪ፣ ተገደፍኪ።

በዚህ ሥራሽ፣ ወጥተሽ ወደቅሽ።

ዐመል፣ ያስወጣል ከመሀል።

በጽባሕ ዘተናገረ ኢይደግም በሠርክ።

ጧት የተናገረውን ማታ አያስታውሰውም።

ምኝና ወረቀት ያስያዙትን አይለቅም። (ተቃራኒ)

በቍስለ ዚአሁ ሀዮነ ቍስለነ።

በርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን።

ዐባይ ቢሸፍት ተከዜን በፍልጥ።

ወታደር ባጠፋ ባላገር ይካስ።

ቢጽ ለቢጹ ይትራድዖ።

ጓደኛ ጓደኛውን ይረዳዋል።

በሬ እንኳን ለወገኑ በፈርሱ ያጓራል።

አህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም።

ቢጽ ምስለ ቢጹ።

ጓደኛ ከጓደኛው።

ዘመድ ከዘመዱ፣ አህያ ካመዱ።

ግም ለግም፣ አብረህ አዝግም።



www.debelo.org

## የ ግ እ ዝ ም ሳ ሌ ያ ዊ አ ነ ጋ ገ ሮ ች

ባሕ እንተ ጸባብ እንቀጽ።

  በጠበበው በር ግቡ።

ቤዛ ነፍሱ ለሰብእ ጥሪተ ብዕሉ።

  ሀብት ለሰው ቤዛው ነው።

  የሌለው፣ መዳኛም የለው።

ብላዕ በሐፈ ገጽከ።

  ጥረህ ግረህ ብላ።

  ሢሠሩ እንደ ባሪያ፣ ሲበሉ እንደ ጌታ።

ብእሲ ማእምር ኀዘን ለነፍሱ።

  አስተዋይ ሰው ያዝንበት እያጣም።

  ከጭንቅ ሁሉ የሚከፋው ብዙ ማወቅና

  ምንም ማድረግ አለመቻል ነው።

ብእሲት አዛል (እዚዝ) አክሊል ለምታ።

  መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት።

  ሚስቱ ደግ፣ ለንዴ ራቱ፣ ወይራ እንጨቱ፣

  ደስታ ነው ቤቱ።

  ለንዴ ራቱ፣ ወይራ እሳቱ፣ማለፊያ ሚስቱ፣

  ምን ሠርግ ይሄዳል ሠርግ አለ ቤቱ።

ብእሲ እኩይ የኃብል እእርክተ።



www.debelo.org

## ኢ ን ጋ ሪ ም ሳ ሌ ዘ ግ እ ዝ

  ክፉ ሰው በነገር ሥራ ወዳጆችን ይለያያል።

ብእሲ ወብእሲት እሐዱ አካል እሙንቱ።

  ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው።

  ባልና ሚስት ካንድ ባሕር ይቀዳሉ።

ብእሲ ጠዋይ ይልዕክ እከየ።

  ጠማማ ሰው ክፋትን ከሁሉ ያደርሳል።

ብዙኃን መኳንንት እለ ወድቁ ውስተ ምድር፤

ወቦ ባሕታዊ ዘተቀጸለ ክሊለ።

  በዚህ ዓለም በመከራ የወደቁ ባለሥልጣኖች

  ብዙ ናቸው፤

  ዘውድ የተቀዳጀ ባሕታዊም አለ።

ብዙኃን እለ ወድቁ በሐጺን፤

ወአኮ ከመ እለ ወድቁ በልሳን።

  በጦር ተደብድበው የወደቁ ብዙዎች ናቸው፤

  ነገር ግን በነገረ ሠሪ እንደበት እንደጠፉት አይሆኑም።

  ጦር ከፈታው፣ ወሬ የፈታው።

ብዙኃን ይመውኡ።

  ብዙዎች ያሸንፋሉ።

  አንድነት ኃይል ነው።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

የሕዝብ ሀብቱ፣ አንድነቱ።

የትውልድ ጉልበቱ፣ ኅብረቱ።

አንድ ጣት ቁንጫ አይገድልም።

ብዙኃን ጽዉኣን፤ ወኅዳጣን ኅሩያን።

የተጠሩ ብዙዎች፣ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው።

ልጁ ሲሞት መቶ አምሳ፣ እሱ ሲሞት አምሳ።

ብየ ሥልጣን ሳዕለ ኵሉ ዘኮነ ወእኮ ኵሉ ዘይበቍዓኒ።

ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ሁሉ ግን አይጠቅመኝም።

ብፁዓት መካናት ዘኢወለዳ።

ያልወለዱ ብፁዓት ናቸው።

የወለደ፣ አበደ።

ልጅ ያለ፣ ልጅ አከለ።

ከመውለድ ሰነፍ፣ መጨንገፍ።

የከፉ ልጅ እናት ሁልጊዜ ታዝናለች።

ለባት ወልዳ ዐቃቢነት።

ብፁዓን ገባርያነ ሰላም።

የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው።

«ሰማይ ተቀደደ» ቢሉት «ሽማግሌ ይሰፋዋል» አለ።

ብፁዕ ዘይሁብ እም ዘይነስእ።



www.debelo.org

## እንጋሪ ምሳሌ ዘግእዝ

ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ በፁዕ ነው።

እንኳን ማብላት መብላት አለ።

ብፁዕ ዘይደበድባ ለከርሡ።

ሰውነቱን የሚንከባከባት ብፁዕ ነው።

ማንን ብየ ጽጌን ጠምኪት!

ጣረ ለከርሡ።

ቦ አለ ተሐርዩ እምከርሠ እሞሙ።

ከናታቸው ማህጸን ጀምሮ የተመረጡ አሉ።

ይታደሏል እንጅ፣ ይታገሏል?

ሰው ይለፋል፣ ዕድል ይሠራል፡

ቦ ጊዜ ለኵሉ።

ለሁሉም ጊዜ አለው።

ዘመን ያነሳው ታላቅ ዜማ እንቅርት ያፈርጣል። አለቃዘነብ

ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል።

✝

ተልዒልየ ተትህትኩ፤ ወተመነንኩ።

ተከብሬ ሳበቃ ተዋረድኩ።

ወጣ ወጣና እንደሸንበቆ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ።

ተሰአሎ ለአቡከ ይነግረከ፤ ወለሊቃውንቲከ ይዜንዉከ።

አባትህን ጠይቀው ይነግርሃል፤
መምህሮችህንም ጠይቃቸው ያስረዱሃል።
መጠየቅ፣ ያደርጋል ሊቅ።
ተከብሮ፣ ያደርጋል ደንቆሮ።

ተበአስ በእንተ ጽድቅ እስከ ለሞት።
ለእውነት እስከ ሞት ድረስ ተጋደል።
እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር።

ተንተንኩ ለወዲቅ፤ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ።
ልወድቅ ተንገዳገድኩ፤ እግዚአብሔር ግን አነሣኝ።
ሳይደግስ አይጣላ።
እንጀራው ቢሳሳ፣ ከወጡ አሰው ካሳ።

ተአምሑ በበይናቲከሙ በአምሐ ቅድሳት።
በተቀደሰ ሰላምታ እጅ ተነሳሱ።
ከመሳሳም ዝምድና ይቀራል።

ተዓቀብ እምጸላእትከ አሐደ ጊዜ፤
ወተአቀብ እም ፍቁርከ ፲፻ ጊዜያተ። ወልደ ሕይወት እንፍራንዝዌ
ከጠላትህ አንድ ጊዜ፣ ከወዳጅህ ሺህ ጊዜ ተጠንቀቅ።
ከጠላቴ እኔ እጠበቃለሁ፤
ከወዳጅ ጠላት አንተ ጠብቀኝ።



www.debelo.org



ተዘከሩ መኳንንቲከሙ፣ ዘነገሩከሙ ቃለ እግዚአብሔር።
የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯችሁን፣
አስተማሪዎቻችሁን አስታውሱ።
የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው በሻሽ፤
ኋለኛው እንዳይሸሽ።

ተገኀሥ እም እኩይ፤ ወግበር ሠናየ።
ከክፋት ራቅ፤ መልካምንም አድርግ።
ክፉ ለራሱ፣ ደግ ለራሱ።

ተፋቀሩ በበይናቲከሙ።
እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።
ፍቅር ካለ ቡጢ እራት ነው።

ተፋቅሮሰ ፍጹም ሕግ።
ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።
ፍቅር ያሥራል፤ ዕውቀት ያስከብራል፤
ጥበብ ያኮራል።

ትበልዒ ወኢትጸግቢ።
ትበያለሽ ግን አትጠግቢም።
ሆድ አየሁ አይልም።

ትንቢት ይቀድሞ ለነገር።

ድርጊትን ትንቢት ይቀድመዋል፡፡

ትንቢት ይመራል፤ ልጓም ይገራል፡፡

ትእቢትሰ ጸሩ ለክርስቶስ፡፡

ትቢተኛ የክርስቶስ ጠላት ነው፡፡

ሰው ሊወድቅ ሲል ይኮራል፡፡

ኩራት፣ እራት ነው፡፡ (ተቃራኒ)

ትውልደ ጻድቃን ይትባረኩ፡፡

የደጋግ ሰዎች ልጆች ይባረካሉ፡፡

የማሽላ ዘር፣ ከነአገዳው ቸር፡፡

## ኀ

ኀላፊ ንብረት፣ ከመ ጽላሎት፡፡

ሀብት እንደ ጥላ አላፊ ነው፡፡

ሀብት የጠዋት ጤዛ ነው፡፡

ዓለም አላፊ፣ መልክ ረጋፊ ነው፡፡

ዓለም አታላይ፣ እንደ በቅሎ ኮብላይ፡፡

ኀበ ሀሎ መዝገብክሙ ሀየ ይሄሉ ልብክሙ፡፡

ሀብታችሁ ባለበት ልባችሁም ይገኛል፡፡

ማንን ይዞ፣ ጉዞ?

ኀበ ሀሎ ገደላ ሀየ ይትጋብኡ አንስርት፡፡



www.debelo.org



ጥንብ ባለበት አሞሮች ይሰበሰባሉ፡፡

ጥንብ ባለበት አሞራ ይዞራል፡፡

ኀዘን ስአብዳን፤ ወፍስሐ ስጠቢባን፡፡

ሀዘን ለሰነፎች፣ ደስታ ለብልሆች፡፡

ብልህ የዓመቱን፣ ሞኝ የዕለቱን፡፡

ያረሰማ ኀበዝ እርፍ የነቀነቀ፣

ወፍጮው እንዳጓራ መስከረም ዘለቀ፡፡

ኀጺን ለኀጺን ይትባልኆ፡፡

ብረት ብረትን ይስለዋል፡፡

እሾህን በእሾህ፡፡

ያገሩን ሠርዶ ባገሩ በሬ፡፡

ኃይሉ ለሰብእ በአምጣነ ቆሙ፡፡

የሰው ኃይሉ በቁመቱ ልክ፡፡

ያባቱ ልጅ፡፡

ኅዳጣን ይትጌበሩ፤ ወብዙኃን የዐርፉ፡፡

ጥቂቶች ይሠራሉ፤ ብዙዎች ይሰበሰባሉ፡፡

በስማም ወልድ፣ ሲያዙኝ አልወድ፣

ሲሰጡኝ መጉመድ፡፡

ኀድጉ አበሳ ስቢጽክሙ፡፡

የወንድማችሁን በደል ተዉለት፡፡

ሲበድሉ ማሩኝታ፣ ሲበደሉ ይቅርታ፡፡

ሲታጠቡ ከክንድ፣ ሲታረቁ ከሆድ፡፡

ኅድጋ ለመዓት ወግድፋ ለቁጥዓ፡፡

ብስጭትን ተዋት፤ ቁጣንም ጣሉት፡፡

ብስጭት፣ ትርፉ ሽበት፡፡

ኅድግዎሙ ለሕጻናት ይምጽኡ ኀቤየ፡፡

ሕጻናትን ተዉአቸው ወደኔ ይምጡ፡፡

ከልጅ አትጫወት፣ ይወጋሃል በእንጨት፡፡ (ተቃራኒ)

ኅድግዎሙ ለምዉታን፤ ይቅብሩ ምዉታኒሆሙ፡፡

ሙታንን ተዉአቸው፤ ሙታኖቻቸውን ይቅበሩ፡፡

ሙታንን ከማመስገን፣ ሕያዋንን ማስተንተን፡፡

ነ

ነባህነ ነባህነ ከመ ዘኢነባህነ ኮነ፡፡

ጩኸን ጩኸን እንዳልጮህን ሆን፡፡

ለፍቶ መና፡፡

አመድ አፋሽ፡፡

ነገሥት ያፈቅሩ ጽልሕዋነ ወመደልዋነ፡፡ዘርዓ ያዕቆብ አክሱማዊ

ገዥዎች ግብዞችንና ሸንጋዮችን ይወዳሉ፡፡



www.debelo.org



ነገረ አማጽያን ኀየለነ፡፡

የነገረኞች ወሬ በጠበጠን፡፡

ነገረኛ፣ ታሞ አይተኛ፡፡

ነገረኛ ሰው ከቤቱ አይሞትም፡፡

ነገረኛ ናቸው፤ አጥልቃችሁ ቅበሯቸው፤

የተነሡ እንደሆን ብዙ ነው ጣጣቸው፡፡

ነገሬ ዘርቅ፡፡

ተራ ወሬ አሉባልታ፡፡

ነፍስ ርኅብት መሪርኒ ጥዑመ ያስተርእያ፡፤

የተራበች ነፍስ መራራው ሁሉ ጣፋጭ ይመስላታል፡፡

ረሃብ ወጥን ያጣፍጣል፡፡

ነፍስየ ትጻእ ምስለ ኢሉፍላውያን፡፡

ከኢሉፍላውያን ጋር ነፍሴ ትውጣ፡፡

ነፍስ ጽግብት ጸቃውዓ መዓር ትሜንን፡፡

የጠገበች ነፍስ የማር ወለላ ትረግጣለች፡፡

ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዉ አኃው ኅቡረ፡፡

እነሆ ወንድሞች ተባብረው ሲኖሩ መልካም ነው፡፡

ለምና ፈትል ካልተዋሃዱ አያበሩ፡፡

ሲተባበር ግም እንኳን ያምራል፡፡ አለቃ ገብረ ሐና

ንሕነ ነአምር ግብሮን ለቆራብት።

የቆራቢዎችን ተግባር እኛ እናውቃለን።

አመንዝራ ካሏት ብትቆርብም አያምኗት።

«የቁርበቶችን ተግባር እኛ እናውቃለን» አለ ጅብ።

ንሥኣ ወብልዓ ለእንታክቲ መጽሐፍ።

አንካ ይችን መጽሐፍ ብላት።

አልመህ ፍጭ፤ አልመህ ተኩስ።

ሸማን ጠምዞ ያሰጧል፤ እህልን አሳምጦ ይውጧል።

መጽሐፍና ተማሪ፣ ቀለበትና ድሪ።

ንቃህ መዋቲ።

የተኛህ ንቃ

በር በሩን ያዘው።

ንባብ ይቀትል፤ ወትርጓሜ ያሐዩ።

ንባብ ይገላል፤ ትርጓሜ ያድናል።

ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል።

ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል።

ንነግርሂ ወኢንዘብጥ።

እንናገራለን እንጅ አንማታም።

ንገረው! ንገረው! እንቢ ካለ መከራው ይምከረው።



www.debelo.org



ንዋይ ከመ እግዚኡ።

ገንዘብ እንደጌታው ነው።

ሰው እንደ ቤቱ፣ ልጅ እንደ አባቱ።

ቅርንጫፉ፣ እንደ ዛፉ።

ሰው ቁመቱን አይቶ ደጃፉን ይሠራል።

ንዋይከ በቅድሜከ።

ገንዘብህን ከፊትህ አትለይ።

ሚስትና ዳዊት፣ ከብብት።

ገንዘብ ከእጅህ፣ ፍርድ (ዳኛ) ከደጅህ።

ንግር ወኢታርምም።

ተናገር ዝም አትበል።

ዝምታ ወርቅ ነው። (ተቃራኒ)

ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ነገር።

ወደ ቀደመው ነገር እንመለስ።

ዙሮ ዙሮ ከቤት፣ ኑሮ ኑሮ ከመሬት።

## አ

አልቦ በቍዔት በከሚተ ኀሊናየ። ዘርዓ ያዕቆብ አክሱማዊ

የልቤን ብናገር ጥቅም የለውም።

ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

አልቦ ክዱን ዘኢይትከሰት፤ ወአልቦ ኅቡእ ዘኢያስተርኢ።

የማይገለጥ ሽሽግ የማይታይ ሥውር የለም።

አልቦ ዘያበርህ ማኅቶተ ከመ ያንብራ ታሕተ ከፊር።

መብራት አብርቶ እንቅብ የሚደፋበት የለም።

ለማን ብየ ጽጌን ጠምኳት!

አልቦ ዘይእህዝ እርፈ ወየሐርስ ድኅሪተ።

ዕርፍ ይዞ ወደ ኋላ የሚያርስ የለም።

አልቦ ገብር ዘየዐቢ እም እግዚኡ፤

ወአልቦ ረድእ ዘየዐቢ እም ሊቁ።

ከጌታው የሚበልጥ አገልጋይ፣

ከመምሩ የሚበልጥ ተማሪ የለም።

ልጅ ቢሮጥ አባቱን አይቀድምም።

አልቦ ገብር ዘይክል ተቀንዮ ለክልዔ አጋእዝት።

ለሁለት ጌቶች ሊገዛ የሚችል አገልጋይ የለም።

ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ ላይ አይወጣም።

እሐቲ ይእቲ ለእማ ።

ለእናቷ አንዲት ናት።

አንድ ለናቱ።

ትንሽ (አንድ) ያላት፣ እንቅልፍ የላት።



www.debelo.org

## እንጋሬ ምሳሌ ዘግእዝ

እሐደ ቀለመ ዘነገረከ ይኩን ከመ አቡከ፤

ክልዔተ ቀለመ ዘነገረከ ይኩን ከመ ፈጣሪከ።

አንድ ቀለም የነገረህ እንደ አባትህ፣

ሁለት ቀለም የነገረህ እንደ ፈጣሪህ ይሁንልህ።

እሐደ ይኩን ቃልክሙ፤

እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ።

ቃላችሁ አንድ ይሁን፤

እዎ ከሆነ እዎ አይደለም ከሆነም አይደለም በሉ።

እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር።

እቃኒ ዘውስተ ዕፀ ሊባኖስ ለአከ ኀበ ዕፀ ቄድሮስ ዘውስተ

ሊባኖስ እንዘ ይብል ሀቦ ወለተከ ለወልድየ ትኩኖ ብእሲተ

የሊባኖስ ኵርንችት ልጅህን ለልጄ ሚስት

እንድትሆነው ስጠው ብሎ ወደ ሊባኖስ ዝግባ ላከ።

ልብ እንቅርት ይመኛል።

አቅረብኩ ለከ እሳተ ወማየ፤ ደይ! እዴከ ኀበ ዘፈቀድከ።

እሳትና ውሃ አቀረብኩልህ፤

እጅህን ወደምትሻው ስደድ።

የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ።

አቅድሙ ለንቀክሙ።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ስንቃችሁን አስቀድሙ።

ሰንቅ ያሰው ጦም አያድርም፤

ዋስ ያሰው አይታሠርም።

አበውኒ ኢታስተቆጥዑ ውሉደክሙ።

አባቶች ልጆቻችሁን አታስቆጡ።

ጠሪታው ወይ ባዩን አስቆጣው።

ሰልጅ ጥሬ። (ተቃራኒ)

አብዝኆ መጻሕፍት ያዘነግእ ልበ።

መጻሕፍትን በብዛት ማንበብ ዝንጉነትን ያመጣል።

እጅግ መሠልጠን መስረቅ ያመጣል፤

እጅግ መብሰል ማረር ይጠቅሳል።

አብድ ይነውም በጊዜ ማእረር።

ሰነፍ በእዝመራ (በሥራ) ጊዜ ይተኛል።

ሰነፍ ሥራ ሲያይ ወደጎን ይሄዳል።

አነ አዐብዮ ሰአቡየ ዕዝን፣ ደኃራዊ ዘበቈልኩ ቀርን።

በኋላ የበቀልኩ ቀንድ አባቴን ጆሮን እበልጠዋለሁ።

ፊት የወጣን ጆሮ በኋላ የወጣ ቀንድ በለጠው።

ከመምሩ፣ ደቀመዝሙሩ።

አነ ዘጳውሎስ፣ ወአነ ዘአጵሎስ፣ ወአነ ዘኬፋ።



www.debelo.org

## አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

እኔ የጳውሎስ፣ እኔ የአጵሎስ፣ እኔ የኬፋ።

መሰያየት ሞት ነው።

ድር ቢያብር፣ አንበሳ ያሥር። (ተቃራኒ)

አንብብዋ ሰመልእክት፤ እም ጥንታ እስከ ተፍጻሜታ።

መልእክቲቱን ከመጀመሪያዋ እስከ መጨረሻዋ

አንብቧት።

ነገርን ከሥሩ፣ ውሃን ከጥሩ።

አሰባብሰው ቢያርሱ፣ ባሬም ይመስሱ።

አንተ ኰኵሀ!

አንተ መሠረት ነህ!

አንትሙሰ ኅሡ እንተ አፍአ

ወእንተ ውስጡስ የአምር እግዚአብሔር።

እናንተ የሳዩን መርምሩ፤

የውስጡን እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው።

አባ ሳዩ ዳባ፣ ውስጡ ደባ።

አንትሙ ተሐውሩ ግድመ ግድመ፤

አነኒ አሐውር ግድመ ግድመ።

እናንተ ግራ ግራውን ትሄደሳችሁ፤

እኔም ግራ ግራውን እሄዳለሁ።

ሲጠሩህ ዝም በል፤ ሳይጠሩህ አቤት በል፤
ነገሩ እንዲዘናበል።
ተንኮለኛ መበለት በጾም ዶሮ፣ በፋሲካ ሽሮ።

አንዔዋ ለኀልፈታ አንፈ ሄሴሜት ታጼኑ።
አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሸታለች።
የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም።

አክብር አባከ ወእመከ።
አባትና እናትህን አክብር።
እናት አባት ሳሉ ቀሊል።
እናት ለልጇ ሙት ናት።
የአባት ባለጌ፣ የገንዘብ አሮጌ የለውም።
አባት ሳለ አጊጥ፤ ጀንበር ሳለ ሩጥ።

አኮ ለዘሮጸ ባህቱ ለዘበደረ።
ለሮጠ አይደለም ለቀደመ እንጅ።
የሮጠ አመለጠኝ፤ የበላ ቀደመኝ።

አኮ በሲበት አላ በአእምሮ።
በሽበት አይደለም፤ በማስተዋል እንጅ።
ቢከፍቱ ተልባ።
አድሮ ቃሪያ።





የትልቅ ትንሽ።

አኵቴቶሙ ዕረፍቶሙ፤ ዕረፍቶሙ አኵቴቶሙ።
እረፍታቸው ማመስገናቸው፣
ማመስገናቸው እረፍታቸው ነው።
ከቅዱሳን አፍ ምስጋና፣
ከሰማይ ላይ ደመና አይታጣም።

አድኅን ርእሰከ።
ራስህን አድን።
ክራስ በላይ ንፋስ
ራስን ይዞ ልጅን፣ ልጅን ይዞ ወዳጅን።

አጽንእ ዘብከ ከመ አልቦ ዘይነሥእ አክሊለከ።
ጸጋህን ማንም እንዳይወስድብህ፣
ያለህን አጥብቀህ ያዝ።
ብልጥ ልጅ የያዘውን እየበላ ያለቅሳል።

አፉሁ ለጻድቅ ይትሜህር ጥበበ።
የደግ ሰው አፍ ጥበብን ይማራል።
አፍ ሲያርፍ ወዳጅን ያማል። (ተቃራኒ)

አፍቅር ቢጸከ ከመ ነፍስከ።
ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ።

www.debelo.org

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ሰውን ሲወዱ ከነንፍጡ ነው።

አፍትን ርእሰከ ለካህን።

ራስህን ለካህን አሳይ።

አድፍህን በውሃ፣ በደልህን በንስሐ።

በቁስ ተናዝዝ፤ በዘመድ ተገነዝ።

አፍኒ ወልብኒ ኅቡረ ይእመኑ።

አፍም ልብም በአንድነት ይመኑ።

በልብ አምኖ ባፍ መንኖ። (ተቃራኒ)

ከወገብ በላይ ታቦት፣ ክወገብ በታች ጣዖት። (ተቃራኒ)

አፍ ይጼውእ ለሞት።

አፍ ሞትን ይጠራል።

በአፍ ይጠፉ፣ በለፈለፉ።

ሎሌ ሲከብር ጌታውን ይከሳል።

ኢተሀቡ ፍኖተ ለሠይጣን።

ለሠይጣን በር አትስጡት።

ለልጅ ጥርስህን፣ ለዝንብ ቁስልህን አታሳይ።

ኢታልምድዎ ወኢትክልእዎ።

አታስለምዱት፤ አትከልክሉት።

አታልምዳቸው፤ አትከልክላቸው።



www.debelo.org

## እንጋሬ ምሳሌ ዘግእዝ

መጀመሪያ ባልዘፈንሽ፣ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ።

ኢታትህት ርእስከ ለብእሲ አብድ።

ለሰነፍ ሰው ራስከን ዝቅ አታድርግ።

ተዋርዶ ቢያላዩት ህብት የጌታ ያድራል።

ኩራት እራት ነው።

ኢታንሥእ ዘኢያንበርከ።

ያላስቀመጥከውን አታንሣ።

የሰው ወርቅ አያደምቅ።

የወደቀን አንሳ የሞተን ቅበር። (ተቃራኒ)

ኢታንክር ዘንተ ዘይብእስ ህሉ።

የባስ አለና ይህን አታድንቅ።

ከድጡ ወደማጡ።

ትሻልን ሰድጀ ትብስን አመጣሁ።

የባሰ አለና አገርክን አትልቀቅ።

ኢታድልዉ ለገጸ ሰብእ።

የሰው ፊት አይታችሁ አታዳሉ።

ሰው ሰው ነው።

ኢታፍቅሩ ወርቀ ወኢብሩረ።

ብርና ወርቅን አትውደዱ።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ሰገቢህ ተንገብገብ! (ተቃራኒ)

ኢትህሚ ሰብአ ውስተ ቤትከ፤

እስመ ያፌ ሰማይ ያወጽአ ሰነገርከ።

በቤትህ ውስጥ እንኳ ቢሆን ሰውን አትማ፤

ነገርህን የሰማይ ወፍ ያወጣብሀልና።

ከአፍ የወጣ አፋፍ።

ሰውን ሲያሙ ጤፍ ቀድሚያ ሰብልቦ ነው።

ኢትልበሱ ልብሰ ሐራ።

የማይገባችሁን ልብስ አትልበሱ።

ሰንበሌጥ ሰቤት ቀሚስ ለሴት።

ሰንበሌጥ ለቤት ቀሚስ ሰባሰቤት።

የሰው ወርቅ፣ እያደምቅ።

ኢትማየ ሰእኩይ በእኩይ፤ አላ በገቢረ ሠናይ።

ክፉን በክፉ አታሸንፈው መልካም በመሥራት እንጅ።

ክፉ ሰራሱ፣ ደግ ሰራሱ።

ኢትርአይ ግርማ ርእየቱ ሰኤልያብ።

የኤያልያብን ግርማ ሞገስ አትይ።

ፊት አይተህ አታድላ።

ሳሰው ቅንጭብ ያረግዳል። (ተቃራኒ)



www.debelo.org

## እንጋሬ ምሳሌ ዘግእዝ

ኢትርፍቅ ውስተ ርእሰ ምርፋቅ።

ከላይኛው መቀመጫ አትቀመጥ።

እንዳቅምሽ አልሚ።

ኢትስርቁ ትብል ወሰሲከ ትሰርቅ።

አትስረቁ ትላሰሀ፤ አንተ ግን ትዘርፋሰሀ።

ጅብ ከማይታወቅበት ሀገር ሂዶ

ቁርበት አንጥፉልኝ አለ።

ኢትስተይ ማይ እራቁ፤

እላ ቶስሀ ወይን በእንተ ህማመ ከብድከ።

ውሃ ብቻ አትጠጣ፤

ሰሰሆድህ ህመም ትንሽ ወይን ጨምር እንጅ።

ኢትቁም እራቀከ ቅድመ ነቢየ እግዚአብሔር፤

በእግዚአብሔር ሰው ፊት ባዶ እጅህን አትቅረብ።

ያሰ መባ፣ ቤተክርስቲያን አትግባ።

ሆድ ባዶ አይወድም።

ኢትቅናዕ ላዕለ እኩያን።

በክፉዎች አትቅና።

ክፉ ሰራሱ ደግ ሰራሱ።

ኢትኅድግ ዐርከከ ዘትካት፤

## የ ግ እ ዝ ም ሳ ሌ ያ ዊ እ ነ ጋ ገ ሮ ች

እስመ ኢይከውነከ ከማሁ ዐርከ ግብት።

ድንገተኛ ወዳጅ እንደሱ አይሆንልህምና

የቀድሞ ወዳጅህን አትተው።

የቀድሞ ወዳጅህን በምን ቀበርከው በሻሽ፤

የኋላው እንዳይሸሽ።

ኢትንእዶ ሰሰብእ ዘእንበሰ ትርዐይ ተፍጻሜቶ።

ሰውን መጨረሻውን ሳታይ አታመስግነው።

አስቀድሞ ማመስገን ኋላ ለሃሜት ያስቸግራል።

ጉድና ጅራት ከወደኋላ ነው።

ኢትኩኑ ከመ መደልዋን።

እንደግብዞች አትሁኑ።

ኢትኩን ጻድቀ ፈድፋደ፤ ወኢትጠበብ ፈድፋደ።

እጅግ ጻድቅ እጅግም ጠቢብ አትሁን።

እጅግ መብሰል ማረር ይጠቅሳል፤

እጅግ መሠልጠን መስረቅ ያመጣል።

ኢትክሉ ተቀንዮ ለእግዚአብሔር ወለንዋይ።

ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።

ሁለት አይወዱ፣ ክመነከሉ አይወልዱ።

ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ከሁለት ዛፍ አይወጣም።



www.debelo.org

## እ ን ጋ ሬ ም ሳ ሌ ዘ ግ እ ዝ

ሁሱ አማረሽን ገበያ አታውጧት።

ኢትክሉ ተቀንዮ ለክልዔ አጋእዝት።

ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም።

ለሁሰተ ጌታ አይገዙም።

ተኳሽ በሁለት ዐይኑ አያነጣጥርም።

ኢትክል ተከብቶ ሀገር፤

እንተ ተሐንጸት መልእልተ ደብር።

በተራራ ላይ የተሠራች ሀገር መሠወር አትችልም።

ግመል ሰርቆ፣ አጎንብሶ አይሄዱም።

ለትኋን ልጓም ማጉረስ፣

ላፈኛ ሰው መመሰስ አይቻልም።

ኢትዛለፍ በማእከለ ሊቃውንት።

በሊቃውንቱ መካከል አትጥቀስ።

ለብልህ አይመክሩ፣ ለአንበሳ አይመትሩ።

ኢትግሥሡ መሊሃንየ ወኢታህስሙ ዲበ ነቢያትየ።

መልእክተኞቼን አታስጨንቁ፤

በነቢያቶቼም ላይ ክፉ አታድርጉ።

ጌታውን ካልናቁ፣ አጥሩን አይነቀንቁ።

ኢትፍርህዎ ለሞት ፍርህዋ ለኃጢአት።

ሞትን አትፍሩት፣ ኃጢአትን እንጅ።
ሞትና አድሜ ቢፈሩት አይቀርም።
ሞትና አድሜ ቢፈሩት አይለቅም።
ላይቀር ሞቱ፣ መንጠራወቱ።
ላይቀር ጣጅው፣ አታብርጅው።
ሞት ላይቀር ፍርሀት፣ ዓመል ላይቀር ቅጣት።
ወይ እኛና ዶሮ አሞራና ሞት፣
ሲመጣ መንጫጫት ሲሄድ መረሳት።

ኢትፍጽሞ ለብዕራይከ ሶበ ታከይድ እክለከ።
እህልክን ስትወቃ የሚያበራየውን በሬ አፍ
አትለጉመው።
በገንዛ ዳቦየ ልብ ልቡን አጣሁት።
አባት ሳም ይለጣል፣ ልጅ አጓት ይነሳል።

ኢየኀድጋ ለህገር ዘእንበለ አሐዱ ሐር።
ህገርን ያለ አንድ ቸር ሰው አይተዋትም።
ሰው ያለበት ሀገር፣ ሰው የሌለበት ዱር።

ኢየአርሩ በለስ እም አስዋክ፤
ወኢይቀስሙ አስካለ እም አሜከላ።
ከእሾህ በለስን አይለቅሙም፤



www.debelo.org



ከደንደርም ወይንን አይቆርጡም።
ከእባብ እንቁላል ርግብ አይፈለፈልም።
ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ።

ኢያስህትከ ላህያ ለብእሲት።
የሴት ውበቷ አያታልህ።
ቆንጆ ሴት፣ ቆንጆ ጭንቅ ናት።
መልክ ታጥቦ አይጠጣም።
ያማረ ፍሬ ሁሉ አይበላም።

ኢይመውዖ ሰሚዕ ለርእይ፡፤
መስማት ማየትን አያሸንፍም።
ማየት ማመን ነው።

ኢይትፈቀድ ምክንያት ለኢአሚን፤
ዳዕሙ ይትፈቀድ ለአሚን። ወልደ ሕይወት እንፍራንዝዊ
ለማመን እንጅ ላለማመን ምክንያት አያሻም።

ኢይክብር ነቢይ በህገሩ።
ነቢይ በህገሩ አይከበርም።
በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል።

ኢይድህን ንጉሥ በዝን ሠራዊቱ።
ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ትረፊ ያላት ነፍስ። (ተቃራኒ)

ኢይጥዕም መዓር ለአድግ ዘእንበለ እጉስታር።

ላህያ ገለባ እንጅ ማር አይጥማትም።

ኢይፈቅድ ይንግርዎ ግእዞ ለሰብእ።

የሰውን ማንነቱን እንዲነግሩት አይሻም።

ለቀባሪው አረዱት።

ኤፍሬም ይበልዖ ለምናሴ፤ ወምናሴ ይበልዖ ለኤፍሬም።

ወንድም ወንድሙን ያጠፋዋል።

ጠርጥር፣ በገንፎ ውስጥ አለ ስንጥር።

እለ መጥባሕተ ያነሥኡ በመጥባሕት ይመውቱ።

በሾተል የገደሉ፣ በሾተል ይሞታሉ።

በሠፈሩት ላዳን፣ በመዘኑት ሚዛን።

በቆረጡት በትር ቢመቱ፣ በመረጡት ዳኛ ቢረቱ፣

በማን ያጉመተምቱ።

እለ ትነብሩ ተንሥኡ።

የተቀመጣቻችሁ ተነሡ።

እለ ከርሦሙ አምላኮሙ።

ሆድ እምላኩዎች።

የበላ ዳኛ፣ የወጋ መጋኛ፣ የሰው መዳኛ።



www.debelo.org

## አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

እለ ጻጹተ ትነጥፋ ወእለ ገመለ ትውህጡ።

ግመልን የምትውጡ፣ ትንኝን የምታጠሩ።

መርፌ የራሷን ቀዳዳ ትታ የሰው ትደፍናለች።

ዐይነት ዐይነቱን ለነፍሴ፣ ግርድ ግርዱን ለፈረሴ።

እመሰ ይትከሃለክሙ ምስለ ኵሉ ሰብእ ተእነው።

ቢቻላችሁስ ከሰዉ ሁሉ ጋር ተወዳጁ።

ዘመድ በየወንዙ ይርባ።

እመሰ ጼው ለስሐ በምንት እንከ ይቄስምዎ?

ጨው አልጫ ቢሆን በምን ያጣፍጡታል?

ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጧል?

ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጧል?

ጨው ለራስህ ብትል ጣፍጥ፤

ያለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሃል።

እመ ተናገርኩ ጽድቀ ለብእ ዛቲ ዓለም ይጸልኡኒ፤

ወከመ ኢይንብብ ህሰተ ኵነኔ ዚእከ ያፈርሃኒ፤

ወእም ኵሉሰ እርምሞ ይኄይስ ወይሤኒ።

እውነት እንዳልናገር የዚህ ዓለም ሰዎች ይጠሉኛል፤

ህሰትም እንዳልናገር ፍርድህ ያስፈራኛል።

ከሁሉም ዝምታ ይሻለኛል።

## የ ግ እ ዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ማወቁን እናውቃለን፤ ብንናገር እናልቃለን።

እመ ወሀበ ብእሲ ኵሎ ንብረቶ ለፍቅር

መንኖ አይሜንንዎ።

ሰው ስለፍቅር ንብረቱን ሁሉ ቢሰጥ

ፈጽሞ አይንቁትም።

የወደደ አበደ።

እመ ይሰድዱክሙ እም አሐቲ ሀገር ጉዩ ኀበ ካልዕታ።

ካንዱ አገር ቢያሳድዷችሁ ወደ ሌላው ሽሹ።

ያልተገኅበጠ ያራል።

እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል።

ቢሄዱ አገር፣ ቢቆፍሩ አፈር፣

ቢተኙ ነገር፣ አይጠፋም።

እም ተናግሮ ይኄይስ አርምሞ።

ከመናገር ዝም ማለት ይሻላል።

ዝምታ ወርቅ ነው።

መታፈር፣ በከንፈር።

ማወቁን እናውቃለን፤ ብንናገር እናልቃለን።

እምነ መንግሥት የዐቢ ክህነት።

ከቤተ መንግሥት ቤተ ክህነት ይበልጣል።



www.debelo.org

## አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

በሰማይ የለ ዱር፣ በቄስ የለ ግብር።

ከጣት ጣት ይበልጣል።

እምነ ረሃብ የኄይስ ኵይናት።

ከረሀብ ጦርነት ይሻላል።

በደነዝ ከመገዝገዝ፣ በስለት መቆረጥ።

እም ንጉሥ እቡድ ይኄይስ ገብር ጠቢብ።

ከሰነፍ ንጉሥ ብልህ አገልጋይ ይሻላል።

ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ።

እም አሐዱ አፍ ይወጽኡ ቡራኬ ወመርገም።

እርግማንና ምርቃት ከአንድ አፍ ይወጣሉ።

ባንድ ራስ፣ ሁለት ምላስ።

ፍየል መንታ ወልዳ አንዱ ለመጽሐፍ፣

አንዱ ለወናፍ።

እም አፈ በሳዒ ወጽአ መብልዕ፤

ወእም አፈ ኃያል ተረክበ ጥዑም።

ከበላተኛ መብል ወጣ፤

ከብርቱም ውስጥ ጥፍጥ ወጣ።

ሌባን ሌባ ቢሰርቀው፣ ምን ይደንቀው!

እም ከመ ተፈስሐ ልብ ይበርህ ገጽ።

ልብ ሲደሰት ፊት ይበራል።

የበላ ቢያብል፣ ፊቱ ይመስከራል።

እም ከመ ኀዘነ ልብ ይጼምን ገጽ።

ልብ ሲያዝን ፊት ይጠቁራል።

ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል

እም ድኅረ ሞቱ ሰሰብእ አልቦቱ ንስሐ።

ሰው ከሞተ ንስሐ የሰውም።

ሰው ከሞተ የሰ ንስሐ፤ ከፈሰስ አይታፈስ ውሃ።

ሙት ምሥጢር አያወጣም።

እም ኵሉ ምግባረ ጽድቅ የዓጽብ ጽሙና፤

ወእም ኵሉ መዓርግ ይትሌዓል ብሕትውና።

ከጽድቅ ሥራ ሁሉ ጭምተኝነት፣

ከማዕረግም ሁሉ ምንኩስና ይበልጣሉ።

እስመ ሰውዳሴኒ ከንቱ ይልዕካ ዝሙት።

ውዳሴ ከንቱን ዝሙት ይልካታል።

ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ኾርግራ ናት ይሏታል።

እስመ ልብሉ ሰሥጋ ሞገሱ።

ልብስ ሰሰውነት ክብሩ ነው።

ስሰ ልብስ፣ ይከበራል ነፍስ።





ስም ከመቃብር በላይ ልብስ ከስውነት በላይ ይውላል።

እስመ መብልዕ ወመስቴ ያስተፋቅር።

ምግብና መጠጥ ያዋድዳል።

አብሮ የበላን ቀዱስ ዮሐንስ አይሽረውም።

እስመ ስሙ ይመረሖ ኀበ ግብሩ።

ስሙ ወደ ሥራው ይመራዋል።

ከስብ ስም ይሽታል።

ስምን መልአክ ያወጣዋል።

እስመ በብዝኃ ጥበብ ብዙኅ ኀዘን።

በጥበብ መብዛት ትካዜ ይበዛል።

እጅግ ስስት፣ ይቀዳል አፎት፤

እጅግ ብልሃት፣ ያደርሳል ከሞት።

እስመ በትህትና ረከበ ልዕልና።

በትህትና ክብርን አገኘ።

ከማጠቢያ ሁሉ ሳሙና፣ ከምግባር ሁሉ ትህትና።

ማሽላ ሲያር ይስቃል፤

ትቢተኛ ሲንደላቀቅ ይወድቃል። (ተቃራኒ)

እስመ በአሐዱ ፍቁር ይስሀብ ካልኡ።

በአንዱ ፍቅር ሌላው ይሳባል።



www.debelo.org

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

የወዳጅ ወዳጅ፣ ወደጅ ነው።

እስመ ተፋቅሮ ይደፍኖን ለኵሉን ኃጣውእ።

ፍቅር በደልን ሁሉ ይፍቃል።

ስለፍቅር፣ በስማም ይቅር።

ሰውን ሲወዱ ከነንፍጡ ነው ።

እስመ ነፍስ ተሐድር በደም።

ነፍስ በደም ታድራለች።

ነፍስ በፈጣሪዋ፣ ሴት ባሳዳሪዋ።

እስመ ነፍስ ተዓጽብ እምሲሲት፤

ወሥጋ የዓጽብ እም ዓራዝ።

ሥጋ (ስውነት) ከልብስ ነፍስም ከምግብ ይበልጣሉ።

ራስ ደህና።

እስመ አልቦ ነገር ዘይስእኖ ለእግዚአብሔር።

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።

ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ።

እስመ እም ቃልከ ትጸድቅ ወእም ቃልከ ትትኳነን።

በአነጋገርህ ይፈረድብሀል፤ ወይም ይፈረድልሀል።

ከአያያዝ ይቀደዳል፤ ካነጋገር ይፈረዳል።

እስመ እምተረፈ ልብ ይነበብ አፍ።



## አንጋሬ ምሳሌ ዘግእዝ

ከልብ ሞልቶ የተረፈውን አፍ ይናገራል።

ልብ ያሰበውን አፍ ይናገረዋል፤

ዐይን ያየውን እጅ ይሠራዋል።

ካልሞላ አይገነፍልም።

ሲሞላ ይፈሳል፤ ሲከር ይበጠሳል።

እስመ ዘአፍቀረ ይጌሥጽ እግዚአብሔር።

እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥጻል።

ላይንና ለወዳጅ ትንሽ ይበቃዋል።

እስመ ፍቅር ከመ ሞት ጽንእት ።

ፍቅር እንደሞት ጽኑ ናት።

ፍቅር መያዣ የሌለውን የስውን ልብ

ማስሪያ ገመድ ነው።

አንድ ሰው በኃይሉ ጥቂት ጊዜ ይገዛል፤

በፍቅር ከሆነ ግን ዓለሙን ሁሉ ለዘላለሙ ይገዛል።

ፍቅር ያስራል፤ ዕውቀት ያኮራል፤ ጥበብ ያስከብራል።

እስመ ኵሉ ለቤቱ ይኄሊ።

ሁሉም ለቤቱ ያስባል።

ራስን ይዞ ልጅን፣ ልጅን ይዞ ወዳጅን።

እስመ ኵሉ ጾሮ ይጸውር።

www.debelo.org

ሁሉም እዳውን ይሸከማል።

ጉንዳን ባልንጀራው ሲሞት

ብቻውን ተሸክሞ ይዞራል።

አመልክን በጉያህ፣ ሰንቅህን ባህያህ።

እስመ ቍር ወረሃብ ያረስዕ ጸሎተ።

ብርድና ረሃብ ጸሎትን ያስረሳል።

ራት የሌለው ቄስ፣ እንደልቡ አይቀድስ።

እንኳን እናቴ ሙታ እንዲያው

አልቅስ አልቅስ ይለኛል።

እስከ ማዕዜኑ ተሐነክሱ በክልዔሆን ጌጋያቲክሙ?

በሁለት ህሳብ እስከ መቸ ታነክሳሳችሁ?

ሁለት ያባረረ፣ አንድም ሳይዝ ቀረ።

እቀትሎ ለኖላዊ ወይዘረዉ እባግዒሁ።

እረኛውን እገድለዋለሁ፤ በጎቹም ይበተናሉ።

አፍንጫን ሲመቱት ዐይን ያለቅሳል።

አብ ሲነካ፣ ወልድ ይነካ።

እንበለ መከራ፣ ኢይትረከብ ጸጋ።

ያለመከራ ጸጋ፣ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝም።

ያለመከራ፣ አይገኝ እንጀራ።





እንበለ ዝናም ደመና፣ እንበለ ንጽህ ምንኩስና።

ያለዝናብ ደመና፣ ያለንጽህና መንኩስና።

የለፍቅር ጸሎት፣ ያለ እንጨት እሳት።

ያለፍቅር ሰላም፣ ያለ ደመና ዝናብ።

እንተ ኢትልህቅ ጣዕዋ ትመርሕ እማ።

የማታድግ ጥጃ እናቷን ትመራለች።

የማታድግ ጥጃ፣ እናቷን በእርግጫ።

እንዘ ቦ ልሂቅ አይትናገር ደቂቅ።

አዋቂ ሽማግሌ እያለ ልጅ አይናገርም።

የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፣ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ።

እንዘ ቦ ርኅብ ውስተ ቤትከ አታውጽእ አፍአ።

ከቤትህ ራብተኛ እያለ ውጭ አውጥተህ አትስጥ።

ራስ ሳይጠና፣ ጉተና።

መጀመሪያ ራስህን የሚያስችል ገቢ ይኑርህ፤

ከዚያ በኋላ ለመመጽወት አስብ።

እኩይ ብእሲ ያወጽእ ለእኪት እም እኪት መዝገበ ልቡ።

ክፉ ሰው ከክፉ ልቡ ክፋቱን ያወጣታል።

የክፉ ሰው ፈስ፣ ዐይን ያፈስ።

ክምጣጣ ጠላ መጠጣት ጅማት ያስቆጣል፤



www.debelo.org

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

የከፉ ሰው ነገርም እንጀት ይበጥሳል። አለቃ ዘነበ

እከል ያጸንእ ኃይለ ለብእ።

እህል (ምግብ) የሰውን ኃይል ያጠነክራል።

የበላ እመለጠኝ፤ የሮጠ ቀደመኝ።

እድ ጽኑእ ብእሴ ያብዕል።

የትጉህ እጅ ታበለጽገዋለች።

እጅህን ባህር ውስጥ ከተት፤ ብታገኝ ዓሣ ታወጣለህ፤

ባታገኝ ታጥበህ ትወጣለህ።

እግዚአብሔር ወሀበ ወእግዚአብሔር ነሥአ።

እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሳ።

የሰጠ ቢነሳ፣ የለበት ወቀሳ።

እጹብሰ እጹብ ውእቱ፤ እሰመ ለእጹብ ትርጓሜ እልቦቱ።

እጹብ እጹብ ነው ለእጹብ ትርጉም የለውም።

እሆ በህሊ።

እሽ ባይ።

እሽ ከተባለ፣ ምን እለ?

### ከ

ከመዝ ንግሩ፤ ወከመ ዝ ግበሩ።

እንዲህ ንገሩ፤ እንዲህ ሥሩ።



www.debelo.org

## ለንጋሬ ምሳሌ ዘግእዝ

«ሜ» ባልኩ፣ ፍየል ከፈልኩ።

ከንቱ ውዳሴ።

የማይገባ ምስጋና።

ኩኑ ቅዱሳነ፤ እሰመ እነሂ ቅዱስ እነ።

እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሶች ሁኑ።

ተመልከት ዓላማህን፤ ተከተል እሰቃህን።

ኩኑ ከመ ይእዜ እለ ተወልዱ ሕጻናት።

ዛሬ እንደ ተወለዱ ሕጻናት ሁኑ።

ልጅነቴ፣ ማርና ወተቴ።

ኩኑ ጠቢባነ ከመ እርእዌ ምድር፤ ወየዋሃነ ከመ ርግብ።

እንደ እባብ ብልህ፣ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ።

ኩን መሃይምነ እስከ ለሞት።

እለከሞት ድረስ የታመንክ ሁን።

ኩን ጠቢብ ለእድውክ

ለባለንጋራህ ብልህ ሁንበት።

ዓሣን መብላት፣ በብልሀት።

ጠላትህ፣ እንደ ዳቦ እኪ.ገምጥህ እትመቸው።

ካህናቲከ ይለብሱ ጽድቀ።

ካህናቶችህ ጽድቅን የጎናጸፉሉ።

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ካህን ይነብር በየማነ ንጉሥ።

ካህን በንጉሥ ቀኝ ይቀመጣል።

ክቡር ሞቱ ለጻድቅ።

የደግ ሰው ሞት የከበረ ነው።

ክቡር እውስቦ በኵሉሄ ወለምስካቡኒ አልቦቱ ሰእበት።

መጋባት በሁሉም ዘንድ ክቡር፤

መኝታውም ቅዱስ ነው።

ኮከብ እም ኮከብ ይኄይስ ክብሩ።

በክብሩ ኮከብ ከኮከብ ይበልጣል።

ከጣት፣ ጣት ይበልጣል።

ወ

ወለሊሁ ሠይጣን ይትሜሰል ከመ መልአከ ብርሃን።

ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክን

እስኪመስል ይለወጣል።

ሰይጣን ሰብልሀቱ መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል።

ወሰእመ ሖርከ ብሔረ ባዕድ ኩን ከማሆሙ።

ሌላ አገር ብትሄድ እንደ እነሱው ሁን።

ሮም ከሄድክ ሮማውያንን ምሰል።

እንደንጉሱ፣ ያጎንብሱ።



www.debelo.org

## አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

እንደ አገሩ፣ ጅብ ይገሩ።

ወለእመ ይሰድድዱከሙ እም እሐቲ ሀገር

ጉዩ ኀበ ካልዕታ።

ካንዱ ሀገር ቢያሳድዷችሁ ወደ ሌላው ሽሹ።

እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል።

ወለደቂቀ መንግሥትሰ ያወጽእዎሙ አፍኣ።

የመንግሥትንም ልጆች ወደ ውጭ ይጥሏቸዋል።

እግዚእ እእምሮ በጠጅ፣ እነወለቡ በደጅ።

ሀገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፤

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ።

ወሙጻኡ ለቅስት የነልቅ በመሐላ።

ክርክር በመሐላ ይዘጋል።

ወምሥጢርከ እስከ ህሎ ውስተ ልብከ ኮነ እሡረ

በፈቃድከ፤ ወለእመ አውጻእኮ እም አፉከ

አንተ ትከውን እሡረ በማእሠሩ። ወልደ ሕይወት እንፍራንዝዊ

ምሥጢርህ በልብህ እስከ ያዝከው ድረስ እሥር ነው፤

ካፍህ ካወጣኸው ግን አንተው ትቀየድበታለህ።

ወቀላለ ኮነት ዘመንየ ከመ ነገረ ዘየእንም።

ዘመኔ ከሸማኔ መወርወሪያ ይልቅ ይቸኩላል።

ሕይወት አጭር ናት።

ወቀደምትኒ ይከውኑ ድኅረ።

ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ።

የቸኮለ አፍሶ ለቀመ።

ፊት የወጣን ጆሮ ኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠው።

ወትወርድ አመጻሁ ዲበ ድማሁ።

ክፋቱ በራሱ ላይ ትደርሳለች።

ደባ ራሱን፣ ስለት ድጉሡን።

ሥራ ለሠሪው፣ እሾህ ላጣሪው።

ወነገረ ቢጽ ኢይጥዕም ሰቢጹ።

የባልንጀራው ሃሰብ ለባልንጀራው አይጥመውም።

አንዱ በአንዱ ሲስቅ፣ ጀንበር ጥልቅ።

ወነገርከ ያዔውቀከ።

አነጋገርህ ማንነትህን ይገልጽብሃል።

ሀሰተኛ በቃሉ፣ ስደተኛ በቅሉ።

ኢትዮጵያዊ መልኩን፣

ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለቅም።

ወኢይጻእ ዐቢይ ነገር እም አፉክሙ።

ክፉ ነገር ካፋችሁ አይውጣ።





ካፍ የወጣ ቃል፣ ከእጅ ያመለጠ እንቁላል።

አፍህን ዝጋ ደጅህን አይደለም።

ወእምኵሉ የዐቢ ተፋቅሮ።

ከሁሉም ፍቅር ይበልጣል።

ፍቅር እግዚአብሔር ነው።

ወክልዔቱ ይሰድድምሙ ለእልፍ።

ሁለቱ ሺህዎቹን ያሳድዷቸዋል።

የሺህ ፍልጥ፣ ማሠሪያው ልጥ።

ወዘአዝለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን።

ትዕግሥትን ያዘወተረ እርሱ ይድናል።

ትዕግሥት ፍሬዋ ጣፋጭ ነው።

ወያገብእ እት እኅዋሁ ለሞት።

ወንድም ወንድሙን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል።

ትልቁ ዓሣ ትንሹን ይውጠዋል።

ትንሹን ደሀ ትልቁ ደሀ አይወደውም።

ወይን ወማኅሌት ያስተፌስሁ አልባበ።

ወይንና ማኅሌት ልብን ያስደስታሉ።

ወይን ያስተፌስሕ ልበ ሰብእ።

ወይን ጠጅ የሰውን ልብ ያስደስታል።



www.debelo.org

ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው።

ወድሶ ለለብእ በዘይደሉ።

ሰውን በሚገባው አመስግነው።

አይዞህ ከመውደቅ ያድናል።

ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጸ ዚአነ ተጽሕፈ።

የተጻፈው ሁሉ እኛ እድንመከርበት ተጻፈ።

ውሂብስ እም ልማድ ውእቱ።

መስጠት ከመልመድ ይመጣል።

የሰመደ ልማድ፣ ያሰርቃል ከማድ።

ድመት መንኩሳ፣ ዓመሏን አትረሳ።

ሌባ ሳመሉ ዳቦ ይልሳል።

ውሂብስ እም ረኪብ ውእቱ።

መስጠት ከማግኘት ይመጣል።

ምን ያምጣ ደሀ፣ ምን ያግሳ ውሃ።

ውሂብ እም ድኅረ ስኢል አስረተ እድ ውእቱ፤

ወውሂብስ ቅድመ ስኢል ፈቲሐ እድ ውእቱ።

ከተለመኑ በኋላ መስጠት እጅ መታሠር፤

ሳይስመኑ መስጠት ልግስና ነው።

አትቁም ያሉት ለማኝ ከስጡት ቁጥር ነው።



www.debelo.org



## ዐ

ዐቃቤ ሥራይ ፈውስ ርእሰከ።

ባለ መድኃኒት ሆይ! ራስህን ፈውስ።

የሳጭን ልጅ ቅማል በላት።

ያባይን ልጅ ውሃ ጠማው።

ዓስምስ ያፈቅር እሊእሁ።

ዓለም የራሱ የሆኑትን ይወዳል።

ግም ለግም፣ አብረህ አዝግም።

ዕብን ዘመነንዋ ነደቅት፣

ወይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማዕዘንት።

እናጢዎች የናቋት ድንጋይ እርሷ

የማዕዘን ራስ ሆነች።

ከቅርብ ያለ ጸበል የልጥ መንከሪያ ነው።

ዕውር ለዕውር ይትማርሖ ወይወድቁ ውስተ ግብ።

ዕውር ዕውርን ቢመራ ተያይዞ ገደል።

ማሽላ ለማሽላ፣ ተያይዞ ቆላ።

ዕውር ኢይባእ ውስተ ዝማሜ ወመላጣ አይሠራዕ ጋሜ።

ዕውር አይዘም፣ መላጣ ጋሜ አይሠራ።

ራስ ተላጭቶ ወሰባ፣ ልባልባ ታጥቆ አዛባ።

## ዘ

ዘላዕለ ነፍሱ ይኤብስ ለመኑ ኄረ ይከውን?

ራሱን የሚነፍግ ለማን ቸር ይሆናል?

ዘልሀቀ በውስቴታ፣ የአምር ሥርዓታ።

በውስጧ ያደገ ሥርዓቷን ያውቃል።

በጥጃየ ባላረሳችሁ፣ የእንቆቅልሼን ፍቺ ባላወቃችሁ።

ዘመሀሩክሙ ዕቀቡ ወዘከመ ምግባሮሙሰ ኢትግበሩ።

ያስተማሯችሁን ተግብሩ፤ የሚሠሩትን ግን አትሥሩ።

ቄስ ያዘዘህን አድርግ፤ ቄስ ያደረገውን ግን አታድርግ።

ዘምር በመጠን!

በልክ ዘምር!

እግርህን በአልጋህ ልክ ዘርጋ።

ዘምስለ ጠዋይ ተጠዋ፤ ወምስለ ኀሩይ ኅሩየ ትከውን።

ከጠማማ ጋር ጠማማ ከቀና ጋር ቀና ትሆናለህ።

ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን ልንገርህ።

ካጋም የተጠጋ ቁልቋል፣ ሲያለቅስ ይኖራል።

ካህያ ጋር የዋለች ላም ፈስ ተምራ መጣች።

ዘረከበ ብእሲተ ኄርተ ረከበ ሞገሰ።

ቸር ሚስት ያገኘ በረከትን አገኘ።



www.debelo.org



የሴት አንዳሻ፣ የጓሮ እርሻ፣ የጎረቤት ውሻ።

ዘለ በዐቅሙ ይበልዕ ጥዑይ ነፍሱ።

መጥኖ የሚበላ፣ ለውነቱ ጤና።

መዛወሪያ ትተህ ብላ።

ዘበውኁድ ምዕመን በብዙኂ ምዕመን።

በትንሹ የታመነ በብዙዉም ይታመናል።

ሲሰርቀኝ ያየሁትን ቢመርቀኝ አላምነውም። (ተቃራኒ)

ዘቦ ብዙኀ ኢያትረፈ፤ ወዘቦ ውኁድ ኢያኀጸጸ።

ብዙ ያለው አልተረፈውም፤

ትንሽ ያለውም አልጎደለበትም።

ዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ፣

ዐስበ ጻድቅ ወእሴተ ጻድቅ ይረክብ።

ጻድቁን በጻድቁ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል።

ያባት እዳ ለልጅ፤ የወፍጮ እዳ ለመጅ። (ተቃራኒ)

ዘኀሠሠ ክልዔ ኢይረክብ አሐደ።

ሁለት የሻ አንድም አያገኝ።

የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች።

ዘኒ ትፈቅዱ ይግበሩ ለክሙ ሰብእ አንትሙኒ ግበሩ

ሎሙ፤ ወዘኒ ኢትፈቅዱ ይግበሩ ብክሙ ኢትግበሩ ቦሙ፡

ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትሹትን አድርጉላቸው፤
ቢያደርጉባችሁ የምትጠሉትንም አታድርጉባቸው።

ዘንስቲት ባቲ፣ ዕረፍት አልባቲ።
ትንሽ ያላት፣ ዕንቅልፍ የላት።
አንድ ያላት ጥርስ፣ በዘነዘና ትነቀስ።

ዘአሀዙ ወርቀ ወዘኢአሀዙ፣ ክልዓሆሙ ኅቡረ ተከዙ።
ወርቅ የያዙትም ሆኑ ያልያዙት በአንድነት አዘኑ።

ዘአልቦ ብእሲት ምንዱብ ውእቱ።
ሚስት የሌለው የተበደለ ነው።
ለማይ ያለ ደመና ብረት፣ ያለ ሴት መሠረት ቤት።
ያለ በሬ መሬት፣ ያለ ሴት ቤት።
የቤት ነፍሷ ሴት ናት። መልእክ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ

ዘአልቦ ኃጢአት ለይገራ።
ኃጢአት የሌለበት ይውገራት።
ከሰው ስህተት፣ ከብረት ዝገት አይጠፋም።

ዘአልቦ ጽልትት።
ማስመሰል የሌለበት።

ዘእልዐለ ርእሶ የኅስር፤ ወዘአትሀተ ርእሶ ይከብር።
ራሱን ከፍ ከፍ ያደረገ ይዋረዳል፤





ራሱን ዝቅዝቅ ያደረገ ይከብራል።

ዘኢተሰምዐ ተሰምዐ፤ ዘኢተገብረ ተገብረ።
ያልተሰማ ተሰማ፤ ያልተደረገ ተደረገ።
አዲስ ነገር የለም። (ተቃራኒ)

ዘኢተገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት።
ለመላእክት ያልተደረገው ለካህናት ተደረገ።
መላእክት የፈሩትን ሞኞች ይደፍሩታል።

ዘኢኮነ ዕድውክሙ በጽክሙ ውእቱ።
የማይቃወመን እርሱ ከኛ ጋር ነው።
የወዳጄ ወዳጅ፣ ወዳጄ ነው።

ዘኢይክል ሠሪዐ ቤቱ
እፎ ያስተሐምም ቤተ እግዚአብሔር?
የራሱን ቤት በሥርዓት ያላደራጀ
ቤተ እግዚአብሔርን እንዴት ያስተዳድራል?
እሷ ክርስትና ሳትነሳ ልታቋቁም ሄደች።
ራስ ሳይጠና፣ ጉተና።
ዐባይ ማደሪያ የሰው ግንድ ይዞ ይዞራል።

ዘኢይፈቅድ ይትገበር ኢይሴሰይ።
ሊሠራ የማይወድ አይብላ።



www.debelo.org

ያለ ሥራ አይበላ እንጀራ፣ ያለ ባላ ቆጥ አይሠራ።

ዘአም ተረፈ ልብ ይነብብ አፍ።

ከልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራል።

የሌለው መዳኛም የለው።

ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ ኢይፍልጥ ሰብእ።

እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው።

ተሰቅሎ የቆየህን አታውርድ፤

ከመሬት ያገኘኸውንም አትስቀል።

ዘከዐወ ደመ ሰብእ ይትከዐው ደሙ።

የሰው ደም ያፈሰሰ ደሙ ይፈሳል።

ብድር፣ በምድር።

ዘክልዔ ልቡ ሀዉክ ውእቱ።

መንታ ልብ ያሰው የታወከ ነው።

ሁለት የተመኘ፣ አንድም አላገኘ።

የመንታ እናት፣ ተንጋላ ትሞት።

ዘወጠነ ይፌጽም።

የጀመረ ይፈጽም።

ጀምሮ መጨረስ፣ አልሞ መተኮስ።

ጀምሮ የማይፈጽም፣ ፈጭቶ የማያልም።





የማያዛልቅ ጸሎት፣ ለቅስፈት።

ዘዐቀበ አስኪቶ የዐቅብ ህይወቶ።

ህፍረተ ሥጋውን የጠበቀ፣ ህይወቱን ጠበቀ።

ዘዘገኑ ወርቀ ወዘኢዘገኑ፣ ክሌዔሆሙ ኅቡረ ኀዘኑ።

ወርቅ ያገኙም አዘኑ፤ ያላገኙም አዘኑ።

ዘየሐውር መርድአ የኀሥሥ ምክንያተ።

የሚሄድ ተማሪ ምክንያት ይሻል።

ሲሻኝ፣ ጢስ ወጋኝ።

ተማሪ ሲለግም እንድ መርፌ ሰአምሳ ይሸከማል።

ዘየዓቅብ አፉሁ ይትመሐፀን ነፍሶ።

አፉን የሚጠብቅ ነፍሱን ይጠብቃል።

ዘያፈቅር ቢጸ ውስተ ብርሃን ይነብር ።

ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል።

ዘይትናገር ዘኢይደልዎ ይሰምዕ ዘይጸልኦ።

የማይገባውን የሚናገር የማይወደውን ይሰማል።

ጠሪታው ወይ ባዩን አለቆጣው።

ዘይከሪ ግበ ለቢጹ ይወድቅ ውስቴቱ።

ለጓደኛው ጉድጓድ የሚቆፍር ራሱ ይወድቅበታል።

አግረ ቀጭን ይሞታል ሲሉት፣

www.debelo.org

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

እግረ ወፍራም ይሞታል።
የእግዜርን ነገር ምኑን አውቀሽው፣
ወይ እኔ እበላው አንች ጋግረሽው።

ዘይወጽእ እም አፉሁ ሰሰብእ ውእቱ ያረኩሶ።
ካፉ የሚወጣው ሰውን ያረክሰዋል።
ተንጋሎ ቢተፉ፣ ተመልሶ ካፉ።

ዘድኅረ መጽአ ዐይነ አውጽአ።
ከኋላ የመጣ ዐይን አወጣ።

ዘጸንአ ዴዴሃ ይበልዕ ፍሬሃ።
ደጅ የጠና ፍሬውን ይበላል።
የቆየ ሰው ከሚስቱ ይወልዳል።
የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል።

ዘጸመወ በዓለም የሐዩ ለዝሉፉ።
በዚህ ዓለም የደከመ ለዘላለም ህያው ይሆናል።
ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ፣
ወፍጮው እንዳንራ መስከረም ዘለቀ።

ዚአከ ለዚአየ፣ ዚአየ ለዚአከ።
አንተ ለኔ እኔ ላንተ።
እከክልኝ ልከክልህ።



## አንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

ዘመድ ቢረዳዳ፣ ችግርም አይጎዳ።

ዛቲ ተግሣጽ ትኩነኒ እምዮም።
ከዛሬ ጀምሮ ይች ተግሣጽ ትዝ ትዝ ትበለኝ።
አይሰመደኝም።

ዝልፎ ለጠቢብ ከመ ይዌስክ ጥበበ፤
ኢትዝልፎ ለአብድ ከመ ኢይጽላእከ።
ብልህን ገሥጸው ጥበብን ይጨምራል፤
ሞኝን አትገሥጸው አንተኑ ይጠላሃል።
ለብልህ ንገረው ምን ይስተው ብየ
ለሰነፍ ንገረው ምን ይሰማ ብየ።
ሳቢውን ግረፈው።

ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ።
የደግ ሰው ሥራ ለዘላለም ይኖራል።
አባት ያበጀው፣ ለልጅ ይበጀው።

ዝ ኩሉ ሥርጋዌ በእንተ አሐዱ ነገር።
ይህ ሁሉ መሽሞንሞን ለአንድ ጉዳይ ነው።
ይህ ሁሉ መጊያጊያጥ፣ ለመላላጥ።

የ

የሀገል ርእሶ ዘኀልያነ ይነሥእ።

www.debelo.org

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

መማለጃን የሚጠላ በሕይወት ይኖራል።
የኃጢአት ክፉ ጉብ፣ የበሽታ ክፉ ተስቦ።
የአምነከ ሰብአ ሶበ ታሜኒ ሎቱ።
ሰው ስትውልስት እምነት ይጥልብሃል።
በጎ አማጭን መጦር፣ ክፉ አማጭን በጦር።
ያኃሥረከ ዘአኅደርኮ፤ ወይዘረክየከ ዘሰቃሕኮ።
ያሳደርከው ያዋርድሀል፤ ያበደርከው ይሰድብሀል።
ባጎረስኩ፣ እጄን ተነከስኩ።
የበላበትን ወጭት ሰባሪ።
ያዕቆብሃ አፍቀርኩ፤ ወኤሳውሃ ጸላእኩ።
ያዕቆብን ወደድኩ፤ ኤሳውን ግን ጠላሁ።
ብዙ ቢወልዱ፣ ሙያውን ዐይተው አንዱን ይወዱ።
ይቤ አጋግ «ከመ ዝኑ ሞት መሪር»
«በውነት ሞት እንዲህ መራር ነውን» አለ አጋግ።
ይብሉ «ሰላም ሰላም!» ወአልቦ ሰላም።
«ሰላም ሰላም!» ይላሉ ሰላም ግን የላቸውም።
ሳር ያልሰጧት ላም
ወተት አምጪ ቢሏት አትሰጥም።
ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር።



## እንጋረ ምሳሌ ዘግእዝ

ሰነፍ በልቡ እምላከ የሰም ይላል።
ውሻ የጌታዋን ጌታ አታውቅም።
ይብእስከ ረጊጽ ውስተ ቀኖት በሲህ።
የመውጊያውን ብረት ብትረግጥ ለአንተው ይብሰብሃል፡
በቅሎ ማሠሪያዋን ቆረጠች፣ አሳጠረች።
ይትወሰወል ሰብእ እም ጊዜ ልደቱ እስከ ጊዜ ሞቱ።
ሰው እስኪሞት ድረስ ሲያመነታ ይኖራል።
እስኪሞቱ ያለ እዳ።
ይኄይስ ህዳጥ ዘበጽድቅ እምብዙኅ ብዕለ ኃጥእን።
በዓመፅ ከተሰበሰበው ከብዙው፣
በሥራ የተገኘው ትንሹ ይበቃል።
እምሳ ዳቦ ከመላስ እንዷን መቆርጠም።
ይኄይስ ብሂም እምነቢበ ህሰት።
ውሸት ከመናገር ዲዳነት ይሻላል።
ያምራል ብሎ ከተናገሩት፣ ይከፋል ብሎ የተዉት።
ይኄይስ ብእሲ ዕጉስ እም ኃያል።
ከኃይለኛ፣ ይሻላል ትዕግሥተኛ።
የውሃ ጠብታዎች ዐለት ይበሳሉ።
ትዕግስት ወቅያኖስን ያደርቃል።

www.debelo.org

## የ ግ እ ዝ ም ሳ ሌ ያ ዊ አ ነ ጋ ገ ሮ ች

ይኄይስ ነዳይ ጥዑይ ሥጋሁ ወፍቱሕ ነፍሱ፤
እምነ ባዕል ዘድውይ ሥጋሁ ወእሱር ነፍሱ።

ሰውነቱ ከታመመና ሆዱ ከታሰረ ባለ ጸጋ
ሰውነቱ ጤነኛ የሆነና ሆዱ የተከፈተ ደሀ ይሻላል።

ይኄይስ አሐዱ እም ፯ ፻፤ ወይኄይስ መዊት ዘእንበለ
ውሉድ እም ወሊድ ወልደ እኩየ።

ከሺዎች ይልቅ አንድ አዋቂ ልጅ ይሻላል፤
ክፉ ከመውሰድም ሳይወልዱ መሞት ይሻላል።
እምሳ ቢወለድ እምሳ ነው ጉዱ፤
የእቶ ---------------- ልጅ ይበቃል እንዱ።

ይኄይስ አርክ ቅሩብ እም እኁ ዘርኁቀ የኀድር።
ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት።

ይኄይስ ፍተ ሐምል ፍቅር ዘቦቱ እመግዝዕ ዘአልህምት።
የጎመን ወጥ በፍቅር መብላት፣
ጥል ባሰበት የሰባ ፍሪዳ ከመብላት ይሻላል።

ይኩን ኵሉ ብእሲ ፍጡነ ለሰሚዕ፤
ወጕንዱየ ለነቢብ ወሰመዓት።
ሰው ሁሉ ለማዳመጥ ፈጣን፤
ለመናገርና ለቁጣ ግን የዘገየ ይሁን።



## አ ን ጋ ረ ም ሳ ሌ ዘ ግ እ ዝ

በጀሮ ጠቢ መንደር ሣር ቅጠሉ አድማጭ ነው።

ይወድስከ እፈ ነኪር ወአኮ አፈ ዚአከ።
ራስክን አታወድስ! ሌላው ያመስግንህ እንጂ።
እራሴን በራሴ፣ እፌን በምላሴ፣
ካላንቆለጳጰስኳት ማን ያንቆለጳጵስልኛል? (ተቃራኒ)

ይደልዎ ለዘያነብብ ይዝክር ስሞ ለበዓለ መጽሐፍ።
አንባቢ የባለ መጽሐፉን ስም ሊያስታውስ ይገባዋል።
ማንን ይዞ ጉዞ።

ይደልዎ አስቡ ለዘይትቀነይ።
ለሠራተኛ ደመወዙ የገባዋል።
የተላከ፣ እፉን ሰከከ።
ሥራ ካልሠራችሁ፣ የት ይገኝ ምሳችሁ?

ይጹም ዐይን፤ ይጹም ልሳን፤ ዕዚንኒ ይጹም።
ዐይን ይጹም፤ አፍ ይጹም፤ ጀሮም ይጹም።
ሰማህ? አልሰማሁም፤ አየህ? አላየሁም።

ደ

ድልዋኒክሙ ንበሩ!
ተዘጋጅታችሁ ኑሩ!
ቅኑት እንደ ገብሬ ጽሙድ እንደ በሬ።

www.debelo.org

ድከምት ቃል ትሰብር እጽመ፡፡

የተሰላለሰች ቃል አጥንት ትሰብራለች፡፡

መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች፡፡

## ገ

ገብእተኒ ወርቅየ፡፡

ገንዘቤን አገኘኧት፡፡

ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል፡፡

የመብል ይደር ያገለግላል፤ የሥራ ይደር ያገነድራል፡፡

ጊዜሁ ለመብልዕ ረሃብ ወለስትይ ጽምእ፡፡

የመመገቢያ ጊዜው መራብ፣

የመጠጫም ጊዜው መጠማት ነው፡፡

ራብ ወጥን ያጣፍጣል፡፡

ጊዜ ለእልኩከ ጸግወኒ ፍታ፤

እስመ ኢየአምር ሰብእ ዘትወልድ ሳኒታ፡፡

የሰው ልጅ ነገ የሚሆነውን አያውቅምና

በሰመንኩህ ጊዜ የዕለት እንጀራየን ስጠኝ፡፡

የዛሬን ሰቀባሪ፣ የነገን ሰፈጣሪ፡፡

ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሀሔር፡፡

እግዚአብሔር የሥራ ጊዜ አለው፡፡



www.debelo.org



ለሰው ወዳጁ ጊዜ ነው፡፡ . . . ጊዜም ማለት

የእግዚአብሔር ሀሳብ የሚፈጸምበት ነው፡፡ ሰለሺ አየለ

ጌሰምሰ ትጌሲ ሰርእሳ፡፡

ነገ ሰለ ራሷ ታስባለች፡፡

የድኅነት ቀን ዛሬ ነው፡፡

ግብር ዘአልቦ ምጣኔ ገዐር ውዕቱ፡፡

ልክ የሌለው ሥራ ብክነት ነው፡፡

ሲበዛ ማርም ይመራል፡፡

## ጠ

ጠቢብ ገብር ይሜብል እግዚኡ፡፡

ጥበበኛ ባሪያ ጌታውን ይገዛል፡፡

ፍየል በግርግር እናቱን ይሰራል፡፡

ጥበብ ትትበድር እምወርቅ፡፡

ከገንዘብ ጥበብ ትመረጣለች፡፡

ገንዘብ ያስገድላል፤ ዕውቀት ያስከብራል፡፡

የገንዘብ ሥር የለውም፡፡

ጥበብ ያስከብራል፤ ሀብት ያስጨፍራል፡፡

ጥበብ ትኄይስ እመኵሉ መዛግብት፡፡

ከሀብት ሁሉ ጥበብ ትበልጣለች፡፡

ፍቅር ያሥራል፤ እውቀት ያኮራል፤

ጥበብ ያስከብራል።

## ጸ

ጸላእተከሙ አፍቅሩ።

ጠላቶቻችሁን ውደዱ።

ጸሎቱ ሰመስተቀይም ኢውክፍት ቅድመ እግዚአብሔር።

የቂመኛ ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት

ተቀባይነት የለውም።

ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት።

ያለፍቅር ጸሎት፣ ያለ እንጨት እሳት።

ጸሎቱ ሰመስተቀይም ከመ ዘርዕ ዘወድቀ ማዕከለ እሰዋክ።

የቂመኛ ጸሎት ከእሾህ ላይ እነደ ወደቀው ዘር ነው።

ዘወትር እየቀባጠረ ከሚጸልይ ሰው፣

ሲነጋ የሚንጫጩ ወፎች ይሻላሉ። አለቃ ዘነብ

ቂም ይዞ ጸሎት፣ ጭድ አዝሎ ወዘት።

ጸጋ በዲብ ጸጋ።

በጸጋ ላይ ጸጋ።

በበረከት ላይ በረከት፣ በሰንበት ላይ ደብረ ዘይት።

ጸማ ከናፍር።



www.debelo.org



ጉንጭ አልፋ።

ጸድቅሰ ይምሕር ወይሁብ።

ደግ ይራራል፤ ይሰጣልም።

ደግ ሰው ሲሰግስ፣ እንደፏፏቴ ያርስ።

ጽጋብ ያመጽእ ግብረ ቅንጻዌ፤ ወቅንጻዌ ያፈደፍድ ደዌ

ጥጋብ ያዘልሳል፤ ዝላይም ስከፋ ሕመም ያጋልጣል።

ካልጠገቡ አይዘሉ፣ ካልዘለሉ አይሰበሩ።

ረሃብን ያማርራል ሰው፣ ቁንጣንን ባይቀምሰው።

## ፀ

ፀሩ ለከርሥ አፍ።

የሆድ ጠላቱ አፍ ነው።

የሆድ ጠላቱ አፍ፣ የዐይን ጠላቱ እጅ።

ያገር ልጅ የቂጥ እከክ ነው።

## ፈ

ፈታሒ በጽድቅ ኮናኒ በርትዕ።

እውነት ፈራጅ ቅን ገገር።

እራትና መብራት ዳኛና ፍትፍት።

ፍሬ ከናፍር።

የንግግር ፍሬ ቃል።

ፍዳ ሳኃጥአን ዕሴት ለጻድቃን፡፡

ለኃጥአን ቅጣት፣ ለጻድቃን ሽልማት፡፡

## ፐ

ፓፓ ዘኢይስሕት፡፡

ፓፓዉ አይሳሳቱም፡፡

ከጳጳሉ በላይ ሃይማኖተኛ፡፡

## ኮ

ኵሉ ማእምር፣ ይገብር በምክር፡፡

ዐዋቂዎች ሁሉ ተማክረው ይሠራሉ፡፡

የተማከሩበት ፈስ አይሸትም፡፡

ኵሉ ቡሩክ፡፡

ሁሉ መልካም፡፡

አልጋ በአልጋ፡፡

ኵሉ ነፍስ ይሴብሖ ለእዚአብሔር፡፡

ነፍስ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግናል፡፡

ወደሽን ቆማጢት ንጉሥ ትመርቂ፡፡፡፡

ኵሉ ንጹሕ ለንጹሓን፡፡

ለንጹሖች ሁሉም ንጹሕ ነው፡፡

ኵሉ ከንቱ፡፡



www.debelo.org



ሁሉም ከንቱ ነው፡፡

«ነበር» እንጅ «ይኖራል» የሚባል ነገር የለም፡፡

ኵሉ ዐረየ ወኀቡረ አለወ፡፡

ሁሉም ተባብሮ ከፋ፡፡

ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ፡፡

ኵሉ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይትገዘም፤

ወውስተ እሳት ይትወደይ፡፡

መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤

ወደ እሳትም ይጣላል፡፡

የሚዛንን አባይ ለእሳት፣ የዳኛን አባይ ለሠንሠለት፡፡

ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ፤

ያለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል፡፡

ኵሉ ዘነፍስ፣ ይበሊ ከመ ልብሰ፡፡

ለው ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል፡፡

ለውና እንጨት ተሰባሪ ነው፡፡

ለውን የሚያስረጅ ሀሳብ፣ ልብን የሚያሰረጅ ለብላብ፡፡

ኵሉ ዘገብራ ለሠናይት ይረከብ ሠናየ፡፡

መልካም የሠራ መልካም ነገር ያገኛል፡፡

ቸር ተመኝ፤ ቸር እንድታገኝ፡፡

ኵሉ ይሤኒ ለእመ ንሤኒ ንህነ።

እኛ ጥሩ ከሆን ሁሉም ነገር ጥሩ ይሆናል።

ኵሉ ይኄሊ ትካዘ ርእሱ።

ሁሉም የራሱን ጭንቅ ያስባል።

ኵሉ ጻድቅ በጊዜ ርቱዕ።

በመልካም ጊዜ ሁሉም ደግ ይሆናል።

ኵሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንኡ (ግበሩ)።

ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ።

## ጐ

ጕንዱየ እብጽሕ እገሪከ ኀበ አርክከ፤
ከመ ኢይጽገብከ፤ ወኢይጽላእከ።

እንዳይሰለችህ፣ እንዳይጠላህም
የባልንጀራህን ቤት አታዘውትር።
አትመላለስ ትሰለቻለህ፤ አትጥፋ ትረሳለህ።

ጕየያ ለፍትወተ ውርዙትከ።

የወጣትነት ፍላጎትህን ሽሽት።
ለስሜትህ ልጓም አብጅለት።



www.debelo.org



# ምርቃት

### ዘእምላኪየ

ዲያቆናተ ቻይና መቅደስ ጠቢባነ እእዳው መጽኡ፣
እንዘ ይብሉ በቃለ ማኅዘኒ ወዜማ ዘሰምዑ፣
«ሰላ ትንብሩ ሕዝብ ዘኢትዮጵያ ተንሥኡ!»

### ትርጉም

የቻይና ቤተ መቅደስ የእጅ ጥበበኞች ዲያቆናት፣
ባዳመጡት ዜማና ባሳዛኝ ቃል፣
«የተቀመጣችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ተነሱ!»
እያሉ መጡ።

### ምሥጢር

ዲያቆናት በቅዳሴ መሀል በሀሳብ ከጸሎተ ቅዳሴው የተነጠለው አስቀዳሽ ወደ ጸሎቱ እንዲመለስ «የተቀመጣችሁ ተነሡ!» እያሉ ያዜማሉ። እንዲሁም ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ቻይናውያን ባለሙያዎች መንገዱን፣ ድልድዩን፣ . . . ሲሠሩ ከበው የሚያዩአቸውን ኢትዮጵያውያንን ሁሉ «ዝም ብላችሁ አትቁሙ! ተነሡ! ሥራ ሥሩ!» አሏቸው ይላል የቅኔው ርቃቂ።

### የደም ልክ

እየተደመረ . . . እየተቀነሰ፣
እየተባዛና . . . እየተካፈለ፣
ሂሳብ መዝገባችን በተወራረሰ፣
ያንዱ ደሙ በዝቶ ያንዱ ባላነሰ።

### ሁሉን አስተምሩኝ

መዳፍ የማታህል የእንጀራ ብጣቂ፣
በሰፊ ሰፌድ ላይ ቢሰጡት ተማሪ፣
«ይችንማ እመይቴ እንዲያው ምን ሳድርጋት?»
ቢላቸው እመይቴም በፈገግታ እያዩት፣
«ብላታ! ጉረሳት! ምንድነው ምትለኝ!
የተማሪ ነገር ሁሉን አስተምሩኝ!»

### ፍንዳታ

መቃብር ባልገባም
በሰቅሶ በዋይታ፣
እርግጥ ነው ሙቻለሁ
የፈነዳሁ ለታ።



www.debelo.org



## የቃላት መፍቻ

ሳዳን - ቁና መስፈሪያ።
ልባልባ - በሐር የተጠለፈ የሴቶች ሱሪ።
ሥርጋዌ - ሽልማት። (ሠርገወ - ሸሰመ)
ቀድሚያ - ጤፍ፣ ገብስ፣...የታጨደበት መሬት ቃርሚያ።
ቅኑት - የታጠቀ።
ቆራብት - ቆራቢዎችና ቁርበቶች (በግእዝ የስዋስው ደንብ የረባ)
በገንዛ - በራሴ ።
ተቸበበ - እጆቹን ሞልቶ ያዘ።
ትቀየድበታለህ - ትታሠርበታለህ።
እባባ - የከብቶች እበትና ሽንት።
እግዚእ አእምሮ - በቅዳሴ ጊዜ ንፍቅ (2ኛ) ቄስ የሚጸልየው ጸሎት።
ወለቡ - የዜማ ተማሪ የሚማረው የዜማ ዓይነት።
ወለከንቢያ - ክዳን።
ወዘት - እሳት መሞቅ
ዘተረከ - ወጋ።
ዘንዘረጡ - የዲያቆን ተወራጅ።
ያባውን - የሸሸገውን። (ኀብአ - ሸሸገ)
ያገነድራል - የውካል፤ ያስቸግራል።
ደወለ - ተማጸነ፤ እድኑኝ አለ።
ድጉስ - የሰይፍ፣ የጎራዴ ሽፋን፤ ማጎደር።
ጉቾ - ትልቅ ጣሳ።
ጽሙድ - የተጠመደ።

# ዋቢ መጻሕፍት


መሐሪ ትረፌ(ሊቀ ሊቃውንት) (ተርጓሚ)። 1951። *ፆቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት።*

ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይምኖት(አሳታሚ)።1955። *ብሉይ ኪዳን። አሥመራ*፤ በኮከበ ጽባሕ ቤተ ማኅተም።

ዝኒ ከማሁ። 1974። *መጽሐፈ ነገሥት። አሥመራ*፤ ኮከበ ጽባሕ ቤተ ማኅተም።

ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ሊቀ መዘምራን)። 1953። *አንጋረ ፈላስፋ።*

በዕውቀቱ ስዩም። 1995። *ኗሪ አልባ ጎጆዎች።* አዲስ አበባ፤ ቅድስተ ማርያም ማተሚያ ቤት።

ብርሃኑ ገ/ጻድቅ። 1992። *የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ስብስብ*፡ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ደርጅት።

ተስፋ ገ/ሥላሴ(አሳታሚ)። 1987። *መዝሙረ ዳዊት ወጸሎታት። ዘነቢያት።* አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። 1966። *የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም-ዛጕዬ። አዲስ አበባ*፤ ብርሃንና ሰላም፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚ ቤት።

ትንሣኤ ማስተሚያ ድርጅት። 1988። *ወንጌል ቅዱስ ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ዝኒ ከማሁ። 1988። *መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ ከቀድሞ አባቶች ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ዝኒ ከማሁ። *1993። መጽሐፈ ስንክሳር በግዕዝና በአማርኛ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ኅሩይ ወ/ሥላሴ*(ብላቴን ጌታ)። 1963። ወዳጄ ልቤ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዝኒ ከማሁ። 1963። *ለልጆ ምክር ለአባት መታሰቢያ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አእምሮ ወንድምአገኘሁ።1985። *መረቅ።* አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት።

አድማሱ ጀንበሬ *(መልአከ ብርሃን)። 1963። መጽሐፈ ቅኔ።* አዲሰ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)። 1948። *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላትሐዲስ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዘሳሰም በየነ። 1992። *English Amharic Proverbs እንግሊዝኛ - አማርኛ ምሳሌዎች።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።




www.debelo.org

## የግእዝ ምሳሌያዊ አነጋገሮች


ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ(አሳታሚ)። 1924። *ሐተታ ዘርዐ ያቆብ አክሱማዊ ወወልደ ሕይወት እንፍራንዛዊ።* አሥመራ፤ አርቲክራፊኪ ኤሪትሬ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። (አሳታሚ) 1980። *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት።* ኬንያ፣ ናይሮቢ፤ United Bible Societies Africa Regional Centre.

ዮናስ አድማሱና ሌሎች። 1966። *አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ።* ለአርት ፋኩልቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ፤ ያልታተመ።

ዳንኤል ወርቁ።(አሳታሚ) 1995። *መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ።* አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት።


✱የታወቁ አበው ሊቃውንት፣ መምህራንና ታላላቅ ሰዎች በየጊዜው የተናገሯቸው ምርጥና ልዩ ንግግሮች በየተጠቀሱበት ቦታ የየተናጋሪዎቹ ስሞች በቅንፍ ተቀምጠዋል።

✱ የየኔታ ውባገኝ ባንቴ ተጨማሪ ታሪክ፣ የተሸለሟቸው ሽልማቶችና ያስተማሯቸው አንዳንድ የታወቁ መምህራን ወዘተረፈ በ«ትንሣኤ» መጽሔት ቁ. 83 1977ዓ.ም. ዜና ሊቃውንት አምድ ይገኛል።



www.debelo.org